# የጳውሎስ ነገረ—መለኮት

## ትምህርት ሦስት
## ጳውሎስና የተሰሎንቄ ሰዎች

# The Heart of Paul's Theology
## Lesson Three
## Paul and the Thessalonians

ተርጓሚ፡ እሸቴ በለጠ
Translator: Eshete Belete

THIRD MILLENNIUM MINISTRIES
Biblical Education. For the World. For Free.

# ማውጫ


1. **መግቢያ**
2. **ዳራ**
   - ሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞ
   - በተሰሎንቄ የነበሩ ችግሮች
     - ስደት
     - የሐሰት መምህራን
     - ክርስቲያናዊ እኑዋኑዋር
3. አወቃቀርና ይዘት
   - 1ኛ ተሰሎንቄ
     - ሰላምታ/የስንብት ሰላምታ
     - ምሥጋና
     - የጳውሎስ አለመኖር
     - መመሪያዎች
   - 2ኛ ተሰሎንቄ
     - ሰላምታ/መዝጊያ
     - ምሥጋናና ማበረታቻ
     - የጳውሎስ ጸሎት
     - መመሪያዎች
4. ነገረ–መለኮታዊ አመለካከት
   - ትምህርተ–ድነት
     - ያለፈ ድነት
     - የወደፊት ድነት
     - የአሁን ድነት
   - ግብረ–ገብ
     - የድነት ሂደት
     - ስነ–ምግባራዊ አንድምታ
   - ታሪካዊ ስፍራ
5. ማጠቃለያ

## 1. መግቢያ

በቅርቡ፣ በአንድ ወንድ ልጁ የዩኒቨርሲቲ ምረቃ ፕሮግራም ላይ ስለተገኘ አባት ታሪክ ሰማሁ፡፡ ከሥነ-ስርዓቱ በኋላ፣ አባትየው በኩራት ወደ ልጁ ጠጋ ብሎ፣ “እንግዲህ በቀሪው ዘመንህ ምን ልታደርግ አቅደሃል፣ ልጄ?” ሲል ጠየቀው፡፡ ተመራቂውም በእጅጉ ፈገግ ብሎ፣ “አየህ አባቴ፣ ስለወደፊቴ ብዙ አስቤበታለሁ፣ እንደማስበውም ከዚህ በኋላ በቀጥታ ወደ ጡረታዬ እገባለሁ” ብሎት አረፈ፡፡ አንግዲህ አብዛኞቻችን ከዚህ ወጣት ተመራቂ ጋር እንመሳሰላለን፡፡ ሆኖም ግን እያንዳንዱ ሰው ሃላፊነት እንዳለበትና ከጡረታም በፊት ለበርካታ ዓመታት በብርቱ መሥራት እንደሚገባው ያውቃል፡፡

ይህ ጉዳይ በጣም እንግዳ እንደሆነብን ዓይነት፣ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን የነበሩ አንዳንድ ክርስቲያኖች አስተሳሰብም ከዚያ ወጣት አስተሳሰብ ጋር ይመሳሰል ነበር፡፡ ለክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ እጅግ ቀናዒ ከመሆናቸው የተነሳ በዚህ ዘመን ለክርስቶስ የመኖርን ነገር እርግፍ አድርገው ትተውት ነበር፡፡

የጳውሎስ ነገረ-መለኮት ከተሰኘው ተከታታይ ትምህርታችን ይህን ሦስተኛውን ትምህርት፣ “ጳውሎስና የተሰሎንቄ ሰዎች” የሚል ርእስ ሰጥተነዋል፡፡ በዚህ ትምህርት፣ በተሰሎንቄ የነበሩ ጥቂት ክርስቲያኖች የክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ እጅግ ቅርብ ነው ብለው በማመናቸው ምክንያት በጣም ከባድ ችግር ፈጥረው እንደነበር እንመለከታለን፡፡ ደግሞም ጳውሎስ ለዚህ የተዛነፈ እምነት እንዴት ምላሽ እንደሰጠም እናያለን፡፡

ጳውሎስና የተሰሎንቄ ሰዎች ተሰኘው ጥናታችን በሦስት ክፍሎች ይከፈላል፡፡ በመጀመሪያ፣ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ዳራ እንመረምራለን፡፡ ሁለተኛ፣ የ1ኛ እና የ2ኛ ተሰሎንቄን አወቃቀርና ይዘት እንቃኛለን፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ የጳውሎስ ደብዳቤዎች ከማእከላዊ ነገረ-መለኮታዊ አመለካከቱ መካከል አንዱን ማለትም፣ ስለ ነገረ-ፍፃሜ ያለውን አስተምህሮ እንዴት እንደሚገልጡ እናያለን፡፡ አስቀድመን ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈውን መልእክት ዳራ እንመልከት፡፡

## 2. ዳራ

በዚህ ተከታታይ ትምህርታችን አጽንዖት እንደሰጠነው፣ ሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶቹን የጻፈው በተለያዩ አብያተክርስቲያናት ለተነሱ የተለያዩ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት ነው፡፡ ስለዚህም፣ 1ኛ እና 2ኛ ተሰሎንቄን በምንመለከትበት ጊዜ፣ አንዳንድ መሠረታዊ ጥያቄዎች መጠየቅ ይገባናል፡፡ በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ውስጥ ምን እየተካሄደ ነበር? ጳውሎስ ለምን ጻፈላቸው?

በመጀመሪያ የጳውሎስን ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ በመመርመር ከዚያም በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተፈጥረው ወደነበሩ ችግሮች ጠልቀን በመግባት ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ እንሰጣለን፡፡ አስቀድመን የጳውሎን ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ እንመልከት፡፡

## ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ

የጳውሎስ ሁለተኛ ሚሲዮናዊ ጉዞ ተመዝግቦ የሚገኘው በሐዋርያት ሥራ 15፡36 እስከ 18፡22 ውስጥ ነው፡፡ በዚያም፣ ጳውሎስ በዘመኗ የግሪክ የተለያዩ ግዛቶች ከመዘዋወሩ አስቀድሞ፣ በዋናነት የተጓዘው በትንሿ እስያ ግዛቶች እንደነበር ሉቃስ ዘግቦልናል፡፡ ልክ እንደ ጳውሎስ የመጀመሪያ ጉዞ ሁሉ፣ ይህኛውም ጉዞ የጀመረው በሶርያዋ አንጾኪያ፣ ሲሆን ምናልባትም በ48 ወይም በ49 ዓ.ም. አካባቢ ነው፡፡ ጳውሎስና በርናባስ አብረው

ለመጓዝ አቅደው ነበር፣ በኋላ ግን በርናባስ ዮሐንስ ማርቆስ አብሯቸው እንዲሆን በመፈለጉ በመካከላቸው አለመስማማት ተፈጠረ፡፡ ጳውሎስ የተቃወመውም ማርቆስ በመጀመሪያ ሚሲዮናዊ ጉዟቸው ትቷቸው ስለነበር ነው፡፡ በመጨረሻም፣ ጳውሎስ ሲላስን የጉዞው ባልደረባ ሲያደርግ፣ በርናባስ ደግሞ ከማርቆስ ጋር ወደ ቆጵሮስ ሄዱ፡፡

ጳውሎስና ሲላስም አስቀድመው በሶርያ በኩል አድርገው ወደ ሴሌውቅያ ወረዱ፡፡ ምንም እንኳን የጎበኟቸውን ከተሞች ለይተን ባናውቅም፣ በእነዚያ ግዛቶች የሚገኙ በርካታ አብያተክርስቲያናትን እንዳበረታቷቸው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ይነግረናል፡፡ ከሴሌውቅያም፣ ወደ ገላትያ በመሄድ፣ ጳውሎስ በመጀመሪያው ጉዞው የተከላቸውን አብያተክርስቲያናት ጎበኙ፡፡ በመጀመሪም በደርቤ ከዚም በልስጥራ ቆይታ አደረጉ፣ በዚያም ጢሞቴዎስ ተቀላቀላቸው፡፡ ከልስጥራ ተነስተውም፣ ወደ ገላትያና ወደፍርግያ አለፉ፡፡

በዚህም ወቅት፣ ጳውሎስ በእስያ ግዛት ውስጥ ማለትም ቢታንያን በስተሰሜን ባደረገ በትንሿ እስያ ምዕራባዊ ግዛት ሊሰብክ ፈለገ፡፡ መንፈስ ቅዱስ ግን አልፈቀደለትም፡፡ ከዚያም ቡድኑ፣ ከፍርግያ ተነስቶ 300 ማይል ወደምትርቀው የወደብ ከተማ ወደ ጢሮአዳ አቀና፡፡ በዚያም ወደ ምዕራብ ፈጥነው ያቀኑበት ምክንያት ግልጽ ሆነ፡፡ ጳውሎስም በህልሙ፣ አንድ የመቄዶኒያ ሰው ናና እርዳን ብሎ ሲለምነው አየ፣ በተቀዳሚነትም ጉዟቸውን በአሁኑ ወቅት በሰሜናዊ የግሪክ ግዛቶች ውስጥ በሚገኙት አካባቢዎች ውስጥ አደረጉ፡፡

ለዚህም ህልም ምላሽ በመስጠት፣ ጳውሎስና ባልደረቦቹ ወደ መቄዶኒያ በመርከብ ተጓዙ፡፡ ፊልጵስዩስ ከመድረሳቸውም አስቀድሞ በናጱሌ በኩል አለፉ፡፡ በዚያም ለጥቂት ጊዜ ቆዩ፣ በርካታ ሰዎችም ወደ ክርስቶስ ተጨመሩ፡፡ ሆኖም፣ በስተመጨረሻ፣ ጳውሎስ ከአንዲት ገረድ ውስጥ አጋንንትን በማስወጣቱ የፊልጵስዩስ ሰዎች አሳሰሩት፡፡ ሆኖም በእስር ቤትም ወንጌል ተሰበከ፡፡ በመንፈቀ ሌሊት፣ የመሬት መንቀጥቀጥ ሆነና የእስረኞች ሰንሰለት ከእጃቸው ወደቀ የእስር ቤቱም ደጅ ተከፈተ፡፡ እስረኞቹ ሊያመልጡ ቢችሉም፣ እነርሱ ግን በየክፍሎቻቸው በመቆየታቸው የእስር ቤቱ ዘበኛ በመጥፋታቸወ ምክንያት ከመቀጣት ተረፈ፡፡ የእስርቤቱም ጠባቂ በተደረገለት በዚህ በጎ ተግባር በመነካት እርሱና ቤተሰቡ በጠቅላላ አመነ፡፡

ሚሲዮናውያኑም ከፊልፓስዩስ ተነስተው፣ በአንፊጶልና በአጶሎኒያ አልፈው ወደ ለሰሎንቄ ደረሱ፡፡ በዚያም ጳውሎስ ለሦስት ሳምንታት በምኩራብ ሰበከ፡፡ በዚህ የወንጌል አገልግሎት፣ በርካታ አይሁዶችና አህዛብ በወንጌል አመኑ፡፡ በዚህም ወቅት ጳውሎስ በእጆቹ እየሠራ ራሱን ይደግፍ ነበር፣ የሚያስፈልገውንም ለማሟላት ከፊልጵስዩስ ክርስቲያኖች ስጦታዎችን ይቀበል ነበር፡፡ እነዚህም እውነታዎች የሚያሳዩን ምናልባት ጳውሎስ በተሰሎንቄ ጥቂት ወራት ቆይታ ሳያደርግ እንደማይቀር ነው፡፡ ሆኖም በስተመጨረሻ፣ አንዳንድ የማያምኑ አይሁድ በወንጌሉ ግስጋሴ በመቅናት በጳውሎስና በሲላስ ላይ ተቃውሞ አስነሱባቸው፣ ወደ ቤርያም እንዲሰደዱ አስገደዷቸው፡፡

በመጀመሪያ ላይም፣ የቤርያ ሰዎች የወንጌልን መልእክት በጉጉት ተቀበሉ፡፡ ወዲያውኑ ግን፣ በተሰሎንቄ ሚገኙ የማያምኑ አይሁድ ነገሩን ሲሰሙ በዚያም በእርሱ ላይ ከተማውን አስነሱበት፡፡ ጳውሎስም እነደገና ተሰደደ፣ በዚህም ወቅት ወደ አቴና አቀና፣ በዚያም እንደ ልማዱ በየምኩራቡ ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን፣ ከኤፊቆሮስና ከኢስጦኢክ የፍልስፍና ወገን ከሆኑት ጋር በገበያ ስፍራም ይሰብክ ነበር፡፡

ጳውሎስ ከአቴና ተነስቶ፣ ወደ ቆሮንቶስ አቀና፣ በዚያም ለአንድ ዓመት ተኩልና ምናልባት ከዚያም በላይ በመቆየት፣ ቤተክርስቲያን ተከለ አሳደገም፡፡ ከዚህም በኋላ፣ ወደ ምስራቅ በማቅናት፣ በክንክራኦስ አጭር ቆታ በማድረግ፣ በትንሿ እስያ ወደምትገኘው ወደ ኤፌሶን በመርከብ ተጓዘ፡፡ ከዚም፣ ወደ ቂሳርያ በመርከብ በመጓዝ ወደ መንደሩ ወደ ሶርያዋ አንጾኪያ ሄደ፣ በመንገዱም በኢየሩሳሌም አልፏል፡፡ ጉዞውም የተጠናቀቀው ምናልባት በ 51 ወይም 52 ዓ.ም. አካባቢ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ጳውሎስ እነዚህን ሁለት ደብዳቤዎች ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈው በዚህ በሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ወቅት ነበር፡፡ እንደ 1ኛ ተሰሎንቄ 3፡1-2 አገላለጽ፣ ጳውሎስ በአቴና በነበረበት ወቅት ጢሞቴዎስ ወደ ተሰሎንቄ በመመለስ በዚያ ያሉ አማኞችን እንዲያበረታታ ልኮት ነበር፡፡ ይህም በ49 ወይም 50 ዓ.ም. አካባቢ ማለትም ጳውሎስና ባልደረቦቹ ተሰሎንቄን ለቅቀው ከወጡ በኋላ ነበር፡፡ ምናልባትም በ50 ወይም በ51 ዓ.ም. አካባቢ ጢሞቴዎስ ሲመለስ ጳውሎስ በቆሮንቶስ ሳይሆን አይቀርም፡፡

በዚያን ጊዜም ጢሞቴዎስ በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተከስተው የነበሩ ብርቱ የግንዛቤ መዛነፎችንና የተፈጠሩ ተግባራዊ ችግሮችን ለጳውሎስ በግልጽ ነገረው፡፡ ጢሞቴዎስም እርሱ ጋ ከደረሰ በኋላ ወዲውኑ ለእነዚህ ጉዳዮች ምላሽ ለመስጠት ሲል ጳውሎስ ከቆሮንቶስ 1ኛ ተሰሎንቄን የጻፈላቸው ይመስላል፡፡ 2ኛ ተሰሎንቄ ግን ከጥቂት ወራት በኋላ፣ ግን ከዚያው ከቆሮንቶስ ተጻፈ፡፡

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፋቸው መልእክቶች ከሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ሰፊ አውድ ጋር እንዴት እንደሚጣጣም ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን የተፈጠሩ ችግሮችን ለየት አድርገን መመልከት ይገባናል፡፡

# በተሰሎንቄ የነበሩ ችግሮች

ጳውሎስን ያሳሰቡት ጉዳዮች ምን ነበሩ? ለተሰሎንቄ ሰዎች አንድ ጊዜ ሳይሆን ሁለት ጊዜ እንዲጽፍ ያደረገው ብርቱ ችግር ምን ነበር? እንደትኛውም ሁኔታ ሁሉ፣ በተሰሎንቄ አርስ በርስ የተሳሰሩ ችግሮች ነበሩ፡፡ ሆኖም ጳውሎስ ለዚች ቤተክርስቲያን የጻፈውን መልእክት ስንመለከት ግን፣ ሦስት ዋና ችግሮች ፊት ለፊት ጎልተው ይወጣሉ፡ በመጀመሪያ፣ የስደት ትግል፤ ሁለተኛ፣ በቤተክርስቲያን የሐሰት መምህራን መነሣት፤ ሦስተኛ ደግሞ፣ የሐሰት መምህራኑ ወደ ቤተክርስቲያን ያመጡት የተግባራዊ የክርስትና አኗኗር ጉዳይ ነው፡፡ አስቀድመን ከስደት ጋር በተያያዘው ጉዳይ ላይ እናተኩር፡፡

## ስደት/መከራ

ጳውሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን ወደ ተሰሎንቄ ይዞ ሲመጣ፣ በዚያ የሚኖሩ አማኞች የብጥብጥ ዒላማ፣ እጅግ ብርቱ፣ ሕይወት ፈታኝ መከራ ውስጥ ነበሩ፡፡ በተሰሎንቄ የነበረውን ሁኔታ ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ 17፡5 የገለጸበትን ሁኔታ አድምጡ፡

> ***አይሁድ ግን ቀንተው ከሥራ ፈቶች ክፉ ሰዎችን አመጡ ሕዝብንም ሰብስበው ከተማውን አወኩ፥ ወደ ሕዝብም ያወጡአቸው ዘንድ ፈልገው ወደ ኢያሶን ቤት ቀረቡ፤ (የሐዋርያት ሥራ 17፡5)***

አይሁድ የወንጌል ተቃዋሚዎች እግጅ ግትሮችና ከከተማ ወደ ከተማ እየተዘዋወሩ ክርስቲያኖችን ሲሳድዱ አህዛብ ሳይቀሩ የክርስትናን እምነት እንዲቃወሙ የሚያነሳሱ ነበሩ፡፡

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈው መልእክት እንደሚያሳየን ጳውሎስ ከተሰሎንቄ ከሄደም በኋላ መከራው ቀጥሎ ነበር፡፡ በ1ኛ ተሰሎንቄ 2፡14-16፣ ጳውሎስ መከራቸውን እንዲህ ገልፆታል፡

> ***እናንተ፥ ወንድሞች ሆይ፥ በይሁዳ የሚኖሩትን በክርስቶስ ኢየሱስ ያሉትን የእግዚአብሔርን ማኅበሮች የምትመስሉ ሆናችኋልና፤ እነርሱ ከአይሁድ መከራ እንደ ተቀበሉ፥ እናንተ ደግሞ ያንን መከራ ከአገራችሁ ሰዎች ተቀብላችኋልና።***

*እነዚያም ጌታን ኢየሱስን ደግሞ ገደሉ ነቢያትንም እኛንም አሳደዱ፥ እግዚአብሔርንም ደስ አያሰኙም፥ ሰዎችንም ሁሉ ይቃወማሉ፥ ሁልጊዜ ኃጢአታቸውን ይፈጽሙ ዘንድ አሕዛብ እንዲድኑ እንዳንናገራቸው ይከለክሉናልና። ነገር ግን ቍጣው ወደ እነርሱ ፈጽሞ ደርሶአል። (1ኛ ተሰ 2፡14-16)*

ጳወሎስ ለመጀመሪያ ጊዜ ወንጌልን በተሰሎንቄ ከሰበከበት ጊዜ አንስቶ መልእክቱን እስከጻፈላቸው ጊዜ ድረስ፣ መከራ በተሰሎንቄ ለክርስቶስ የመኖር የሕይወት ዘይቤ ሆኖ ዘልቆ ነበር፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ በዚያች ከተማ ለሚኖሩ አማኞች ሲጽፍላቸው፣ ስለ መከራውና በእነርሱ ላይ ስለሚያሳድረው ጫና በጣም ያስብ ነበር፡፡

## የሐሰት ነቢያት

የተሰሎንቄ ሰዎች በመከራ ውስጥ በስቃይ ከማለፋቸው ባሻገር፣ ቤተክርስቲያኒቱ በሐሰት ነቢያት ጫና ስርም ወድቃ ነበር፡፡ በአንድ መንገድ፣ ይህ አስገራሚ አይደለም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ፣ በታሪክ ዘመናት ሁሉ፣ ክርስቲያኖች ለረጅም ዘመን በመከራ ውስጥ ሲያልፉ፣ አብዛኛውን ጊዜ ኢየሱስ ዳግመኛ ተመልሶ እንዲመጣና ከስቃያቸው እንዲያሳርፋቸው ይናፍቃሉ፡፡ በቀላሉ ለማስቀመጥ፣ በመከራ ውስጥ የሚያልፉ ክርስቲያኖች ሕይወታቸው ሙሉ በሙሉ በክርስቶስ ዳግም መምጣት ላይ ወደማተኮሩ ያደላል፡፡ ይህ ሕይወት ከተስፋ መቁረጥና ከመከራ ዘለል ያለ ነገር ሲያስከትል፣ ኢየሱስ መጥቶ እኛን ነፃ ወደ ሚያወጣባት ቀን ዐይናችንን እናዞራለን፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ፣ ክርስቲያኖች ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ከልክ አልፈው ግድ ከተሰኙ፣ አብዛኛውን ጊዜ ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ጽንፋዊ አስተሳሰብ ላላቸው የሐሰት መምህራን እና የሐሰት ነቢያት ተጋላጭ ይሆናሉ፡፡ በተሰሎንቄ ሰዎችም ላይ የደረሰው በትክክል ይህ ዓይነቱ ነገር ነው፡፡ የሐሰት መምህራኑ ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ የተሳሳተ እምነት ይዘው ወደ ቤተክርስቲያኒቱ ገቡ፡፡

በተሰሎንቄ የነበሩ የሐሰት መምህራን ምን ያህል ችግር እንደፈጠሩ ለማየት ያስችለን ዘንድ ሁለት መሠረታዊ ጉዳዮችን እንዳስሳለን፡ በሐሰት ነቢያቱና በጳውሎስ መካከል የተፈጠረውና እያደገ የሄደው ግጭት እና የሀሰት ነቢያቱ አስተምህሮ ይዘት ናቸው፡፡ አስቀድመን የሐሰት ትንቢቱን ተግዳሮት እንመልከት፡፡

በ1ኛ እና በ2ኛ ተሰሎንቄ መጻሕፍት ልዩ ልዩ ክፍሎች ውስጥ የሐሰት መምህራኑ የጳውሎስን ትምህርት አትብቀው ይቃወሙ እንደነበር በገሃድ ይታያል፡፡ ለምሳሌ፣ የተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ስለ ነበረችበት ሁኔታ ከጢሞቴዎስ ሪፖርት ሲደርሰው፣ የሐሰት ነቢያቱ ወደ አማኞች ኅብረት ውስጥ በመግባት ከእርሱ አስተምህሮ አንዳንዶቹን በመቃወም እንደተናገሩ ጳውሎስ ተረዳ፡፡ ለዚህ ችግረ ጳውሎስ ከሰጠው ምላሽ አንዱ የተሰሎንቄ ሰዎች የሚሰሙትን ትንቢት በጥንቃቄ እንዲመረምሩ ማሳሰብ ነበር፡፡ በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡20-21 የተናገራቸውን ቃላት አድምጡ፡

*ትንቢትን አትናቁ፤ ሁሉን ፈትኑ መልካሙንም ያዙ፤ (1ኛ ተሰሎንቄ ፡20-21)*

የተሰሎንቄ ሰዎች "ሁሉን እንዲፈትኑ" እና "መልካሙን እንዲይዙ" ጳውሎስ ያዛቸዋል ምክንያቱም የሚቀበሉትን የትኛውንም መመሪያ በትክክል እንዲመረምሩ ይፈልግ ስለነበር ነው፡፡ በቅዱሳት መጻሕፍት እውነት ሆኖ ከተመዘገበው እና ከጳውሎስ ትምህርት ጋር የማይስማማውን ውድቅ በማድረግ ሊይዙ የሚገባቸው መልካሙን ብቻ ነበር፡፡

የሐሰት ነቢያቱ ግን በቀላሉ አልተሸነፉም፡፡ ይልቁኑ፣ የሐሰት ትምህርታቸውንማስተማርና መስበካቸውን ገፉበት፡፡ እንዲያውም፣ የተሰሎንቄ ሰዎች አመለካከታቸውን እንዲቀበሉ ለማድረግ ያስችላቸው ዘንድ በጳውሎስ

ስም የሐሰት ደብዳቤ እስከመጻፍ ድረስ ረጅም ርቀት ተጓዙ፡፡ ጳውሎስም 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-2 ስጽፍ ይህ ስለመሰለው እንቅስቃሴ በጣም የተጨነቀ መሆኑ በግልጽ ይታያል፡

> *ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን። ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-2)*

ጳውሎስ ስለ ሐሰተኛ ደብዳቤው የነበረው ጭንቀት በ2ኛ ተሰሎንቄ 3፡17 እንዲህ ብሎ ሲጽፍም በግልጽ ተቀምጧል፡

> *በገዛ እጄ የተጻፈ የእኔ የጳውሎስ ሰላምታ ይህ ነው፤ የመልእክቴ ሁሉ ማስረጃ ይህ ነው፤ እንዲህ እጽፋለሁ። (2ኛ ተሰሎንቄ 5፡17)*

ጳውሎስ የሚጽፋቸው ደብዳቤዎች በትክክል የእርሱ ለመሆናቸው ምልክት ይሆን ዘንድ ልክ እንደ ፊርማ ያገለግሉ ዘንድ በራሱ የእጅ ጽሑፍ የተጻፉ ቃላትን በደብዳቤው ውስጥ እንደሚያካትት ይጠቅሳል፡፡ ይህንንም የሚያደርገው የተሰሎንቄ ሰዎች በትክክል የእርሱ የሆነውን እንዲለዩና የሐሰት ትንቢቱን እንዳይቀበሉ ነው፡፡

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈውን መልእክት እኛ በምናነብበት ወቅት ከሐሰት ነቢያቱ ጋር የነበረው ግጭት አንድ ሌላ ጉዳይ በውስጣችን ይጫራል ያም፡ እነዚህ የሐሰት ነቢያት የሚያስተምሩት ምን ነበር? ያስተምሩ ስለነበሩት ነገር በጠቅላላ በእርግጠኝነት መናገር አንችልም፣ ሆኖም በተሰሎንቄ ነበረውን ተከታታይ መከራና ጳውሎስ ወደ ተሰሎንቄ ሰዎች የጻፋቸውን ምልእክቶች ይዘት ስንቃኝ ግን፣ የሀሰት ነቢያቱ ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ የጠሳሳተ ግንዛቤ ነበራቸው ብለን መደምደም እንችላለን፡፡ ማዕከላዊ ችግራቸው የነበረው፣ ኢየሱስ በፍጥነት ይመጣል (ወዲውኑ በዚያ ዘመን) ብለው ማመናቸው ነው፡፡ እንዲያውም፣ ለእኛ ነገሩ የማይታመን ቢመስልም፣ አንዳንድ የሐሰት ነቢያት ክርስቶስ ተመልሷል ብለው ያውጃሉ፡፡ 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-3

> *ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለ መሰብሰባችን፥ በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልእክት፦ የጌታ ቀን ደርሶአል ብላችሁ፥ ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን።*
> *ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ከህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና። (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-3)*

በግልጽ እንደሚታየው፣ አንዳንድ የሐሰት ነቢያት የተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ መመለስ አምልጧታል ብለው ያስተምሩ ነበር፡፡ ይህንን አስተሳሰብ እንዳመጡ የሚነገረውም በተሰሎንቄ ማኀበረሰብ አንድ በሞት የለተየና ካቢሩስ ተብሎ ከሚጠራ ጀግና አምልኮ ጋር የተገናኘ ሲሆን፣ የሚያስቡትም ያ ጀግና አንዳንድ ወቅቶች ወደ ዓለም እየተመለሰ ይመጣል ብለው ነው፤ የሐሰት መምህራኑም ይህንን መሳዩን አስተሳሰብ ወደ ክርስትናው እምነት በማምጣት ክርስቶስ ተመልሶ መጥቷል ብለው ለተሰሎንቄ ሰዎች ይነግራሉ፡፡

የእነዚህ ስህተቶች ምንጭ ምንም ይሁን ምን፣ ጳውሎስ የሐሰት መምህራኑን በብርቱ በማውገዝ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች ግን ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ እርሱ የነገራቸውን አጥብቀው እንዲይዙ መመሪያ ይሰጣቸዋል፡፡

## ክርስቲያናዊ አኗኗር

መከራና የሐሰት ትንቢት ወደ ተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን እንዴት እንደገባ ተመልክተናል፣ አሁን ደግሞ እነዚህ ችግሮች በቤተክርስቲያን ላይ እንዴት ተፅዕኖ እንደፈጠሩ የሚያሳዩ ተግባራዊ መገለጫዎችን መመልከት ይገባናል፡፡ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው መልእክት ውስጥ በርካታ አሳሳቢ ነገሮች ተገልጠዋል፣ እኛ ግን በሁለቱ ላይ ብቻ እናተኩራለን፡ ተስፋ መቁረጥና ኃላፊነትን መዘንጋት ናቸው፡፡ አስቀድመን የተሰሎንቄን ሰዎች ተስፋ መቁረጥ እንመልከት፡፡

አብዛኛውን ጊዜ፣ ክርስቲያኖች የክርስቶስ መመለስ በደጅ ነው ብለው በሚያምኑበት ወቅት፣ ኢየሱስ እነርሱ በጠበቁበት መንገድ ሳይገለጥ ሲቀር ተስፋ መቁረጣቸው አይቀሬ ነው፡፡ በተሰሎንቄም፣ በርካታ አማኞች ሕይወታቸውን በጠቅላላ ከክርስቶስ ወዲውኑ የመመለስ ግንዛቤ ጋር አቆራኝተውታል፡፡ ስለ ክርስቶስ ሲሉ መከራ ጠቀብለዋል ብዙም ደርሶባቸዋል፡፡ ሆኖም ወራት እያለፉ ሲሄዱ፣ ተስፋ መቁረጥ ብቻ ሳይሆን፣ ጉዳዩን እጅግ ከፍቶ፣ በርካታ አማኞች አለፉ፡፡ በሕይወት የቀሩት ደግሞ በሞት የተለዩዋቸው አማኞች ዘላለማዊ ዕጣ ፈንታ ያሳስባቸው ጀመር፡፡ ይህ ግራ መጋባት ወደ ጥርጣሬ፣ ጥርጣሬው ደግሞ ወደ ተስፋ መቁረጥ መራቸው፡፡ ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡13-14 ለስለስ አድርጎ እንዴት እንዳረጋቸው እናድምጥ፡

*ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ተስፋ እንደሌላቸው እንደ ሌሎች ደግሞ እንዳታዝኑ፥*
*አንቀላፍተው ስላሉቱ ታውቁ ዘንድ እንወዳለን።*
*ኢየሱስ እንደ ሞተና እንደ ተነሣ ካመንን፥ እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉቱን*
*እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና። (1ኛ ተሰሎንቄ 4፡13-14)*

በሞት የተለዩዋቸው ቅዱሳን በአካል ቢሞቱም፣ በክርስቶስ ግን ሕያዋን ናቸው፣ ክርስቶስም ዳግመኛ ሲመጣ ከእርሱ ጋር አብረው ይመለሳሉ በማለት ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ያረጋግጥላቸዋል፡፡

ተስፋ ከመቁረጡና ከግራ መጋባቱ በተጨማሪ፣ የሐሰት ነቢያቱ መልእክት ኃላፊነት ወደ ጎደለው የአኗኗር ዘይቤ ውስጥ ከቷቸዋል፡፡ በተሰሎንቄ ምን እንደተከሰተ ለመረዳት አስቸጋሪ አይሆንም፡፡ ራሳችሁን በእነርሱ ሁኔታ ውስጥ አስቀምጣች እዩት፡፡ በሚቀጥለው ወር ዓለም ያበቃላታል ብላችሁ ብታምኑ፣ ወደ ሥራ ትሄዳላችሁ ወይስ ቤታችሁን ታድሳላችሁ ወይስ ትምህርት ቤት ትገነባላችሁ? ኢየሱስ በጥቂት ቀናት ውስጥ መለሳል ብላችሁ ከልክ በላይ እርግጠኝነት ከተሰማችሁ፣ መደበኞቹ እንቅስቃሴዎች አላስፈላጊ መስለው ይታያሉ፡፡

በተሰሎንቄ የሆነው ነገር በትክክል ይህንን የሚመስል ነገር ነው፡፡ የሐሰት መምህራኑ አንዳንድ ክርስቲያኖችን በማሳሳት ኑሮን ለማሸነፍ መሥራት አያስፈልግም ብለው አሳምነዋቸው ነበር፡፡ አስተሳሰባቸውም "ክርስቶስ ቶሎ የሚመጣ ከሆነ ስለ ሥራ መጨነቅ ለምን?" የሚል ዓይነት ነበር፡፡

*ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ከፊት ይልቅ ልትበዙ፥ በጸጥታም ትኖሩ ዘንድ ልትቀኑ፥ የራሳችሁንም ጉዳይ ልትጠነቀቁ፥ እንዳዘዝናችሁም፥ በውጭ ባሉት ዘንድ በአገባብ እንድትመላለሱ፥ አንዳችም እንዳያስፈልጋችሁ በእጃችሁ ልትሠሩ እንለምናችኋለን። (1ኛ ተሰሎንቄ 4፡11-12)*

የሚያሳዝነው ግን፣ ወደ ዕለታዊ ጉዳቻቸው በትጋት እንዲመለሱ ጳውሎስ ካሳሰባቸውም በኋላ እንኳን፣ በተሰሎንቄ የነበሩ አንዳንድ አማኞች ግን ወደ ኃላፊነቶቻቸው አልተመለሱም ነበር፡፡ ስለዚህም ጳውሎስ፣ ጉዳዩን እንደገና በ2ኛ ተሰሎንቄ ያነሳዋል፣ ያነሳው ግን ጠንከር አድርጎ ነው፡፡ በ2ኛ ተሰሎንቄ 3፡6-12 እንዲህ ጽፏል፡

*ወንድሞች ሆይ፥ ከእኛ እንደ ተቀበለው ወግ ሳይሆን ያለ ሥርዓት ከሚሄድ ወንድም*
*ሁሉ ትለዩ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እናዛችኋለን።*
*እኛን ልትመስሉ እንዴት እንደሚገባችሁ ራሳችሁ ታውቃላችሁና፤ በእናንተ ዘንድ ያለ*
*ሥርዓት አልሄድንምና፤*

*ከእናንተ ዘንድ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት፥ ሌሊትና ቀን በድካምና በጥረት እየሠራን እንኖር ነበር እንጂ፥ ከማንም እንጀራን እንዲያው አልበላንም።*
*ይህም እኛን ልትመስሉ ራሳችንን እንደ ምሳሌ እንሰጣችሁ ዘንድ ነበር እንጂ፥ ያለ ሥልጣን ስለ ሆንን አይደለም።*
*ደግሞ ከእናንተ ጋር ፡-ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና።*
*ሥራ ከቶ ሳይሠሩ፥ በሰው ነገር እየገቡ፥ ያለ ሥርዓት ከእናንተ ዘንድ ስለሚሄዱ ስለ አንዳንዶች ሰምተናልና።*
*እንደነዚህ ያሉትንም በጸጥታ እየሠሩ የገዛ እንጀራቸውን ይበሉ ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናዛቸዋለን እንመክራቸውማለን። (2ኛ ተሰሎንቄ 3፡6-12)*

ክርስቶስ ዳግመኛ አሁኑኑ ይመለሳል የሚለው የሐሰት ትንቢት የተሰሎንቄን ሰዎች ሰነፍና ሥራ ፈት እንዲሆኑ አድርጓቸዋል፡፡ ሥራፈትነት ደግሞ ለበርካታ ችግሮች መንሥዔ ይሆናል፡፡

ስለዚህ በተሰሎንቄ የነበሩ ችግሮች ፈርጀ ብዙና እርስ በርስ የተሳሰሩ እንደሆነ እናያለን፡፡ መከራው የክርስቶስን ዳግመኛ መመለስ በተሳሳተ መንገድ በቶሎ እንደሆነ አድርገው እንዲረዱት በር ከፈተ፡፡ እነዚህ የተሳሳቱ እምነቶች ደግሞ ተስፋ መቁረጥና ኃላፊነት ማይሰማው የመሆንን ተግባራዊ ችግሮች አስከተሉ፡፡ ጳውሎስም ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፋቸው ደብዳቤዎች እነዚህ ፈታኝ ችግሮች ለመጋፈጥ እንደሚያስችሏቸው ተስፋ ያደርጋል፡፡

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች ለጻፈው ደብዳቤ ዳራ ሊሆኑ የሚችሉ ጥቂት ወሳኝ ጉዳደችን ከተመለከትን፣ አሁን ደግሞ የደብዳቤዎቹን ይዘቶች ወደ መመልከቱ እንሸጋገራለን፡፡

# 3. አወቃቀርና ይዘት

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈው ምንድን ነው? ለተወሳሰቡ ችግሮቻቸው መልስ የሰጠው እንዴት ነው? የዋና ዋና ክፍሎቻቸውን ይዘቶች ጠቅለል አድርገን በማቅረብ ሁለቱንም የተሰሎንቄ መልእክቶች እንዳስሳለን፡፡ በ1ኛ ተሰሎንቄ እንጀምር፡፡

## 1ኛ ተሰሎንቄ

1ኛ ተሰሎንቄ በአምስት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡ አንደኛ፣ በ1፡1 ውስጥ ሰላምታ፤ ሁለተኛ፣ በ1፡2-2፡16 ውስጥ የምሥጋና ሪፖርት፤ ሶስተኛ፣ በ2፡17-3፡13 ስለ ጳውሎስ አለመኖር፤ አራተኛ፣ በ4፡1-5፡22 ጳውሎስ ለቤተክርስቲያን የሰጣቸው መመሪዎች፤ አምስተኛ፣ በ5፡23-28 ስንብት ናቸው፡፡

### ሰላምታ/ ስንብት

ልክ እንደ በርካቶቹ የጳውሎስ መልእክቶች፣ የ1ኛ ተሰሎንቄ የመጀመሪያና የመጨረሻ ክፍሎች አጭርና ቀጥተኛ ናቸው፡፡ ሰላምታው በቀላሉ የሚጠቅሰው ደብዳቤው ለተሰሎንቄ ሰዎች የተጻፈና ጸሐፊውም ጳውሎስ መሆኑን ነው፡፡ ደስ የሚለው፣ ሲላስና ጢሞቴዎስም ባልደረቦች መሆናቸውን ይጠቅሳል፡፡ እርግጥ ነው፣ ሲላስና ጢሞቴዎስ የጳውሎስን የሐዋርያነት ሥልጣን አይጋሩም፣ ስለዚህ ይህ መልእክት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተካተተው በጳውሎስ ሐዋርያዊ ሥልጣን ብቻ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሲላስና ጢሞቴዎስ መጠቀሳቸው የሚያመለክተው ጳውሎስ ይህንን የማይሻር ደብዳቤ የጻፈው ከእውነተኛ ሰብዓዊ አመለካከት እንደሆነ ነው፡፡ የመዝጊያው ክፍል ደግሞ አጭር ነው፣ ቡራኬ፣ የጸሎት ጥያቄ እና የስንብት ሰላምታ ይዟል፡፡ ወደ ሁለተኛ የተሰሎንቄ መልእክት ክፍል

ስንገባ ግን የመጽሐፉን ወሰብሰብ  ያለ ይዘት እናገኛለን፡፡ ይህ ሰፊ ክፍል ጳውሎስ ለእግዚአብሔር ያቀረበውን ምስጋና የያዘ ሲሆን በሦስት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡

## *ምሥጋና*

በመጀመሪያ፣ በ 1፡2-10 ውስጥ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች በመከራ ውስጥ ስለጸኑ እግዚአብሔርን የሚያመሰግን ስለመሆኑ ጳውሎስ ያብራራል፡፡ እንደተመለከትነው፣ የማያምኑት አይሁድ እና አህዛብ በተሰሎንቄ ያሉትን አማኞች ያሳድዱ ነበር፡፡ አማኞቹ ግን ለክርስቶስ ያላቸው መሰጠት አልዋዠቀም፡፡ ይልቁኑ፣ በእርሱ ያላቸው ተስፋ እጠነከረ ሄደ፡፡ ጳውሎስ በ1ኛ ተሰሎንቄ 1፡6-7 ጳውሎስ ስለ እነርሱ እንዴት እንዳመሰገነ እናድምጥ፡

> *ደግሞ እናንተ ቃሉን በብዙ መከራ ከመንፈስ ቅዱስ ደስታ ጋር ተቀብላችሁ፥ እኛንና ጌታን የምትመስሉ ሆናችሁ፤*
> *ስለዚህም በመቄዶንያና በአካይያ ላሉት ምእመናን ሁሉ ምሳሌ ሆናችሁላቸው።*
> *(1ኛ ተሰሎንቄ 1፡6-7)*

የተሰሎንቄ ሰዎች የገጠማቸውን መከራ የተቀበሉት በደስታ ከመሆኑ ባሻገር፣ ታማኝነታቸው ምሳሌነት ያለው ነበር፡፡

በ2፡1-12 ውስጥ፣ ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች ስለ እርሱ ስላላቸው ትክክለኛ እውቀት ያለውን አድናቆት መግለፁን ይገፋበታል፡፡ ይህ ነገር በጣም  አስፈላጊ ነው ምክንያቱም የሐሰት ነቢያቱ በተከታታይነት የጳውሎስን ተነሳስቶ ይፈታተኑ ስለነበር ነው፡፡ በ1ኛ ተሰሎንቄ 2፡9-10 እንዲህ ጽፏል፡

> *ወንድሞች ሆይ፥ ድካማችንና ጥረታችን ትዝ ይላችኋልና፤ ከእናንተ በአንዱ ስንኳ እንዳንከብድበት ሌሊትና ቀን እየሠራን፥ የእግዚአብሔርን ወንጌል ለእናንተ ሰበክን።*
> *በእናንተ በምታምኑ ዘንድ በእንዴት ያለ ቅድስናና ጽድቅ ነቀፋም በሌለበት ኑሮ እንደ ሄድን፥ እናንተና እግዚአብሔር ምስክሮች ናችሁ፤ (1ኛ ተሰሎንቄ 2፡9-10)*

የሐሰት ነቢያቱ ጳውሎስን ዋጋ ለማሳጣት ይጣጣሩ ነበር ያንንም የሚያደርጉት የተሰሎንቄን ሰዎች መጠቀሚያ እንዳደረጋቸውና እነርሱንም እያሳሳተና በእነርሱ ላይ ሥልጣኑን አለአግባብ እየተጠቀመ ነው በማለት ነበር፡፡ ቢያንስ አንዳንድ አማኞችም የሐሰት ወሬዎቹን ማመን እየጀመሩ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት፣ እነርሱ ራሳቸው ፊት ለፊት ስላዩት ምን ያህል ደስተኛ እንደሆነ ይነግራቸው ነበር፡፡ በእርግጥም፣ ያንን ያደረገው የተሰሎንቄ ሰዎች እርሱን በደንብ ስለሚያውቁት የሐሰት ክሱን ውድቅ ሊያደርጉት እንዲችሉ ብሎ ነበር፡፡

በብዙ ተመሳሳይ መንገድም፣ በ2፡13-16 በሚገኘው፣ በሦስተኛው የምስጋና ክፍል፣ የተሰሎንቄ ሰዎች ለእርሱ ስልጣን እውቅና በመስጠታቸው ጳውሎስ ያመሰግናቸዋል፡፡ በ1ኛ ተሰሎንቄ 2፡13 ይህንን ያስቀመጠበትን መንገድ አድምጡ፡

> *ስለዚህም የመልእክትን ቃል እርሱም የእግዚአብሔር ቃል ከእኛ በተቀበላችሁ ጊዜ፥ በእውነት እንዳለ በእናንተ በምታምኑ ደግሞ እንደሚሠራ እንደ እግዚአብሔር ቃል እንጂ እንደ ሰው ቃል አድርጋችሁ ስላልተቀበላችሁት፥ እኛ ደግሞ እግዚአብሔርን ሳናቋርጥ እናመሰግናለን። (1ኛ ተሰሎንቄ 2፡13)*

የተሰሎንቄ ሰዎች የጳውሎስን ትምህርት እንደ እግዚአብሔር ቃል አድርገው መቀበላቸው ለእርሱ ትምህርት ታማኝ ሆነው እንደሚዘልቁና የሐሰት ነቢያቱንም እንደማይቀበሉ እርግጠኝነት እንዲሰማው አድርጎታል፡፡

ጳውሎስ ስለ እነርሱ ያለውን አድናቆት በመግለጽ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች በታማኝነታቸው እንዲዘልቁ ካነሳሳቸው በኋላ፣ ወደ መልእክቱ ሦስተኛ ዋና ክፍል፣ 2፡17-3፡13 ይሸጋገራል፡፡ በዚያም ውስጥ፣ በጉዞው ምክንያት ከእነርሱ ስለ መለየቱ ያነሳል፡፡ ይህም ክፍል በራሱ በሦስት ዐቢይ ክፍሎች ከፈላል፡፡

## የጳውሎስ ከእነርሱ መለየት

በ2፡17-3፡5 ድረስ ጳውሎስ ስ እነርሱ ዘወትር እንደሚያስብና ግድ እንደሚለው ለተሰሎንቄ ሰዎች ያረጋግጥላቸዋል፡፡ ይህንንም የሚያሳያቸው ጢሞቴዎስን እንዲጎበኛቸው ወደ እነርሱ በመላክ ነው፡፡ በ1ኛ ተሰሎንቄ 3፡1-2 ጳውሎስ የተናገረውን እናድምጥ፡

> *ስለዚህ ወደ ፊት እንታገሥ ዘንድ ባልተቻለን ጊዜ፥ በአቴና ብቻችንን ልንቀር በጎ ፈቃዳችን ሆነ።*
> *ስለ እምነታችሁም እንዲያጸናችሁና እንዲመክራችሁ ወንድማችንን የእግዚአብሔርንም አገልጋይ ከእኛ ጋርም አብሮ በክርስቶስ ወንጌል የሚሠራውን ጢሞቴዎስን ላክነው፤*
> *(1ኛ ተሰሎንቄ 3፡1-2)*

እንደ መጋቢ ግድ ከመሰኘቱ በተጨማሪ፣ ጳውሎስ በ3፡6-10 ውስጥ፣ ጢሞቴዎስ ከተሰሎንቄ ይዞለት በመጣው መልካም ወሬ ምክንያት ምን ያህል አድናቆት የሞላበት ደስታ እንደተሰማው ይገልጻል፡፡ ዜናውም፣ አማኞች በእምነታቸው ጸንተው መቆማቸውን እና ሐዋርያው ከእነርሱ መለየቱ እንዳሳዘነው ሁሉ እነርሱም እርሱን በማጣታቸው የተሰማቸው መሆኑ ነው፡፡ ጳውሎስም በሰማው ነገር እጅግ ደስ ስለተሰኘ፣ በ1ኛ ተሰሎንቄ 3፡8-9 እንዲህ ጽፏል፡

> *እናንተ በጌታ ጸንታችሁ ብትቆሙ፥ አሁን በሕይወት እንኖራለንና።*
> *... ከእናንተ የተነሣ ስለምንደሰተው ደስታ ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር በእናንተ ምክንያት ምን ያህል ምስጋና እናስረክብ ዘንድ እንችላለን? (1ኛ ተሰሎንቄ 3፡8-9)*

ጢሞቴዎስ ያቀረበለትን መልካም ዜና መስማቱ የጳውሎስን ጭንቀት ወደ ደስታና ወደ መተማመን ቀየረለት፡፡

በሦስተኛ ደረጃ፣ በ3፡11-13 ውስጥ፣ ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች እንደገና ማየት እንዲችል እግዚአብሔር መንገዱን እንዲያቀናለት በመለመን ለእነርሱም ይጸልያል፡፡

## መመሪያዎች

የዚህ መልእክት አራተኛ ዋና ክፍል ከ 4፡1-5፡22 ድረስ ይዘልቃል፡፡ ከተሰሎንቄ አማኞች አብዛኞቹ ክርስቶስ በቶሎ ይመለሳል ብለው ከማመናቸው የተነሳ ነገር ተዘበራርቆባቸው አሁን በዚህ ዓለም ስለሚኖሩት ኑሮ ምንም ግድ የማይላቸው ሆነዋል፡፡ ስለዚህም፣ ጳውሎስ አሁን ያሉባቸውንና ወደፊትም ሊመጡ የሚችሉትን ችግሮች ለማስወገድ የሚያስችሏቸውን የተለያ መመሪያዎች ይሰጣቸዋል፡፡ የተሰሎንቄ ሰዎች ስለ ኢየሱስ መመለስ ተስፋቸው እንዲሟጠጥ አልፈለገም፣ እርሱ እንዲገነዘቡ የፈለገው ክርስቶስ ወዲውኑ እንደማይመጣ ነው፡፡ እስከዚያው ድረስ፣ ጌታ እንዳዘዛቸው እንዲመላለሱ ይፈልጋል፡፡ ይህ ክፍል በመጠኑ ረዘም ያለ ሲሆን በውስጡም ጳውሎስ የሚሰጣቸውን ዋና ዋና መመሪዎች የያዘውን ዋና አካል በማስከተል አጭር መግቢያም አካትቷል፡፡

በመጀመሪያ፣ 4፡1-2 ክፍሉን ያስተዋውቃል፡፡ ጳውሎስ በዚህ ስፍራ፣ የቀደመውን ትዕዛዙን በመፈጸማቸው የተሰሎንቄ ሰዎችን በጠቅላላ ያመሰግናል፡፡ እንዲያውም፣ የእርሱን መመሪያዎች ያለመታዘዙ ነገር ሊያደላባቸው እንደሚችል

ያውቃል ምክንያቱን ተቃዋሚዎቹ በስውርና አንዳንዴም በይፋ በምድር ምንም ሃላፊነት የለባችሁም እያሉ ከንቱ ነፃነትን ይሰብኩላቸው ስለነበር ነው፡፡ ስለዚህ፣ ጳውሎስ ትምህርቱ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥልጣን እንደያዘ እና የተሰሎንቄን የእርሱን ንግግር ቸል ቢሉ፣ እግዚአብሔር ራሱ እንደሚጠይቃቸው የተሰሎንቄን ሰዎች ያሳስባቸዋል፡፡

ሁለተኛ፣ በ4፡3-5፡22፣ የተሰሎንቄ ሰዎች ራሳቸውን ከኃጢአት በመጠበቅ ለክርስቶስ ያላቸውን ታዛዥነት በበለጠ ሊያሳዩ የሚችሉባቸውን የተለያዩ መንገዶች ጳውሎስ ይጠቅስላቸዋል፡፡ ቀደም ብለን እንደጠቀስነው፣ ጳውሎስ የተለየ ትኩረት የሰጠው በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ውስጥ በሐሰት ትምህርት አማካይነት ሰርገው ደግሞም በይፋ ገብተው በነበሩ ኃጢአቶች ላይ ነበር፡፡

ጳውሎስ በ4፡3-8 ውስጥ ከዝሙት እንዲርቁ በማዘዝ ይጀምራል፡፡ ከታሪክ እንደምንረዳው፣ የዓለም መጨረሻ ቀርቧል ብለው ለሚያምኑ ቡድኖች ምንዝርና መለያቸው ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ እንዲውም ለዚህ ጉዳይ አግባብነት ያለው ምሳሌ የምናገኘው በዚችው በተሰሎንቄ ማኅበረሰብ የሐሰት እምነት ውስጥ ሲሆን፣ ያም ካባሩስ የተሰኘውን ጣዖታቸውን መመለስ የሚያከብሩት የዝሙትን ርኩሰት መለያው ያደረገን በህርይ የተላበሰ አምልኮ በማቅረብ ነው፡፡ ጳውሎስ ይህንን ክፍል የሚደመድመው ከእርሱ ንግግር በስተጀርባ መለኮታዊ ሥልጣን እንዳለ አስረግጦ በመናገርና ትልቅ አጽንዖት በመስጠት ነው፡፡

በ4፡9-10 ውስጥ፣ ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች ስለ ስለ ወንድማማችነት ፍቅራቸው ያመሰግናቸዋል እጅግ አብዝተው እንዲዋደዱም ያበረታታቸዋል፡፡ የዚህ ምዕራፍ አውድ እንደሚያመለክተን ፍቅር የመግለጫው ተጨባጭ መንገዱ አንድ ሰው የሌላው ሸክም እንዳይሆን ለራሱ የሚያስፈልገውን ነገር በርትቶ በመሥራት መሸፈን ነው፡፡

በ4፡11-12 ውስጥ፣ ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች በየዕለቱ ትርጉም ባለው መንገድ በርትተው እንዲሠሩ ያዝዛቸዋል፡፡ አንዳንድ የተሰሎንቄ አማኞች ኢየሱስ በቅርቡ ይመለሳል በሚለው ሃሳብ ክፉኛ ከመነደፋቸው የተነሳ የዕት ከዕለት ሥራቸውን መሥራት አቁመው ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች በጣም ባለጠጋ ካለመሆናቸው የተነሳ፣ በጎ በማድረግ ለምትታወቀዋ የተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን በገንዘብ ረገድ ሸክም ይሆኑ ጀመር፡፡ ከዚያ ባሻገር፣ ስንፍናቸው በማያምኑ ሰዎች ፊት የቤተክርስቲያንን ምሳሌነትና ተዓማኒነት የሚያጠፋ ነበር፡፡

በ4፡13-18 ውስጥ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች በጌታ ሆነው በሞት የተሌዋቸውን የሚወዷቸውን ሰዎች እንደሚያገኟቸውና አብረዋቸው እንደሚሆኑ በማሰብ እርስ በርሳቸው በዚህ ተስፋ እንዲጽናኑ ሐዋርያው ያሳስባቸዋል፡፡ በሚያሳዝን መንገድ፣ በተሰሎንቄ የነበረው የተሳሳተ ትምህርት አንዳንዶች ኢየሱስ ከመመለሱ አስቀድሞ የሞተ ማንም ሰው አይድንም በሚል ፍራቻ ውስጥ እንዲወድቁ አድርጓቸዋል፡፡

በ5፡1-11 ውስጥ፣ ጌታ ተመልሶ ሲመጣ የማይታዘዙትን እንደሚቀጣ እና የታመኑትን ደግሞ ብድራታቸውን እንደሚከፍል ጳውሎስ ቤተክርስቲያኒቱን ያሳስባል፡፡ የክርስቶስ መመለስ ለስንፍናና ለርኩሰት ምክንያት በፍጹም ሊሆን እንደማይችልና ይልቁኑ መመለሱ አማኞች የተቀደሰን ሕይወት እንዲኖሩ የሚያነሳሳቸው እንደሆነ እንዲረዱለት ጳውሎስ ይፈልጋል፡፡

በ5፡12-13 ውስጥ፣ በተሰሎንቄ ያሉ የቤተክርስቲያን መሪዎች ሥልጣን እንዳላቸው ጳውሎስ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡ ትክክለኛውን አስተምህሮ አጥብቀው የሚይዙ እና የሐሰት መምህራንን የሚቃወሙ መሪዎችን ሾሞላቸዋል፡፡ በውጤቱም፣ የተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ከትክክለኛዎቹ መሪዎችና ያለ አግባብ ራሳቸውን ከሾሙ ሰዎች የተቀላቀለ መልእክት ይቀበሉ ነበር፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ ትክክለኛዎቹ መሪዎች የሚያስተምሩትን ትምህርት መከተልና የሐሰት ነቢያቱን ግን እንዲቃወሙ በግልፅ ያስቀምጥላቸዋል፡፡

በተቀሩት ጥቅሶች ውስጥ፣ ጳውሎስ የተለያዩ ርእሶችን ይዳስሳል፣ ሁሉም ግን በዚህ ትምህርት የዳሰስናቸውን የቀደሙ ትምህርቶቹን ለማረጋገጥና የሐሰት መምህራኑ ለፈጠሯቸው ችግሮች ከልክ በላይ ራሳቸውን እንዳይሰጡ ሰዎችን ለማዳን ታስቦ የቀረቡ ናቸው፡፡ በ5፡14 ውስጥ፣ ሰነፎቹን ሰዎች እሹሩሩ ከማለት ይልቅ

ቤተክርስቲያን ልታስጠነቅቃቸው እንደሚገባ ያመለክታል፡፡ ሆኖም ራሱን መደገፍ ያልቻለን ሰው ሁሉ በጅምላ እንዲያገልሉ ግን አልፈለገም፣ ስለዚህ፣ በእውነት ችግረኛ የሆኑትን እንዲረዱ ያሳስባል፡፡ በ5፡15 ውስጥ፣ በሐሰት መምህራኑ ተፅእኖ ስር ወድቀው የነበሩትን አማኞች የማግለሉን አደገኛ ተግባር ክፉን በመልካም እንዲያሸንፍ ሰውን ሁሉ በማዘዝ ይደመድመዋል፡፡ በ5፡16-18 ውስጥ፣ ጳውሎስ በድጋሚ ከንግግሩ በስተጀርባ ያለውን ሥልጣን በማረጋገጥ ቤተክርስቲያን እያለፈችበት ባለው ችግር ውስጥ ደስተኛ እንድትሆን ያበረታታል፡፡ በ5፡19-22 ውስጥ፣ የሐሰት ነቢያቱን መቃወም ማለት አዳዲስ ትንቢቶችንና ትምህርቶችን በጅምላ መቃወም ማለት እንዳልሆነ በግልጽ ያስቀምጣል፡፡ ይልቁኑ፣ ሁሉም ንግግሮች ሊፈተኑና የተሳሳቱት ብቻ ውድቅ ሊደረጉ ይገባል፡፡

ይህ ዝርዝር መመሪያ፣ በርካታ ተግባራዊ ችግሮችን ዳስሷል፡፡ በሁሉም ረገድ፣ የጳውሎስ አስተሳሰብ አዎንታዊ ነበር፡፡ የተሰሎንቄ ሰዎች ብርቱ ነበሩ ጳውሎስም አመስግኗቸዋል፡፡ ግን ደግሞ በእምነታቸውና ለክርስቶስ በሚያቀርቡት አገልግሎት እያደጉ እንዲሄዱ ያሳስባቸዋል፡፡

የ1ኛ ተሰሎንቄን መልእክት በወፍ በረር ዳሰሰናል፣ አሁን ደግሞ ወደ 2ኛ ተሰሎንቄ ይዘትና አወቃቀር እንሸጋገራለን፡፡

# 2ኛ ተሰሎንቄ

ሁለተኛ ተሰሎንቄም እንዲሁ በአምስት ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡ ሰላምታ በ1፡1-2፤ ሌላኛው የምስጋናና የማበረታቻ መልእክት በ1፡3-10፤ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጸለየው ጸሎት በ1፡11-12፤ የጳውሎስ መመሪዎች በ2፡1-3፡15 እና መዝጊያ በ3፡16-18 ናቸው፡፡

## ሰላምታ/መዝጊያ

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈው ሁለተኛ መልእክት የሚጀምረው ልክ እንደ መጀመሪያው ነው፡፡ ሰላምታው አጭርና ቀጥተኛ ሲሆን፣ ደብዳቤውም ለተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን እንደተጻፈ ያመለክታል፡፡ ልክ እንደ አንደኛ ተሰሎንቄ ሁሉ፣ ደብዳቤው ከጳውሎስ ብቻ ሳይሆን ከሲላስና ከጢሞቴዎስም ጭምር እንደተፃፈ ሰላምታው ያብራራል፡፡ አሁን እንደገና፣ ሲላስና ጢሞቴዎስ ግን የማይሻሩና በሐዋርያዊ ሥልጣን እንዳልጻፉ ማሳሰብ ይገባናል፡፡ ቢሆንም፣ የጳውሎስ ጸሐፊነት በደብዳቤው ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ እውነተኛ እንደሆነና መልእክቱ የሚያስተምረውን ሁሉ ልንታዘዝ እንደሚገባ ሥልጣኑ ግድ ይለናል፡፡ እንዲያውም፣ የመልእክቱን አጭር መዝጊያ ስንመለከት፣ ተቀዳሚ ጸሐፊው ጳውሎስ እንደሆነ ግልጽ ያደርግልናል፡፡ ስለዚህም የመልእክቱን ባለሙሥልጣንነት ለማረጋገጥ ጳውሎስ፣ ጳውሎስ ብቻ፣ በደብዳቤው ላይ እንደፈረመ መረዳት እንችላለን፡፡

## ምሥጋናና ማበረታቻ

ምዕራፍ 1፡3-10 ባካተተው፣ በሁለተኛው ክፍል ውስጥ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች በተለይም በመከራ ውስጥ ስላሳዩት ፍቅር ጳውሎስ በድጋሚ ምሥጋናውን ያቀርባል፡፡ በመጀመሪያው ደብዳቤ ዳስሷቸው የነበሩ ጉዳዮችን አስመልክቶ በድጋሚ ቢጽፍላቸውም፣ ጳውሎስ በተሰሎንቄ ሰዎች ሁኔታ እጅግ ተገርሞ ነበር፡፡ እምነታቸው ለብዙዎች ምን ያህል ምሳሌ እንደሆነ እና ስለ መጽናታቸውም በሌሎች አብያተክርስቲያናት ፊት ምን ያህል እንደተመካባቸው በመንገር ያበረታታቸዋል፡፡ በ2ኛ ተሰሎንቄ 1፡4 የጻፈውን እናድምጥ፡

> ***ስለዚህ በምትታገሡበት በስደታችሁና በመከራችሁ ሁሉ ከመጽናታችሁና ከእምነታችሁ የተነሣ በእግዚአብሔር አብያተ ክርስቲያናት ስለ እናንተ ራሳችን እንመካለን። (2ኛ ተሰሎንቄ 1፡4)***

## የጳውሎስ ጸሎት

በ 1፡11-12 ውስጥ በሚገኘው በሦስተኛው ክፍል፣ አዘውትሮ እንደሚጸልይላቸው በማብራራት፣ የተሰሎንቄ ሰዎች በሚያልፉበት ትግል ውስጥ ብቻቸውን እንዳልሆኑ ይነግራቸዋል፡፡ ለክርስቶስ ባላቸው አገልግሎት ታማኝና ፍሬያማ ይሆኑ ዘንድ እግዚአብሔር በውስጣቸው በኃይል እንዲሠራ እርሱ፣ ጢሞቴዎስና ሲላስ ቀንም ሆነ ማታ ይጸልዩላቸዋል፡፡

## *መመሪያዎች*

የተለያዩ *መመሪያዎችን* የያዘው አራተኛው ክፍል፣ ከ2፡1-3፡15 ድረስ የሚዘልቀው ክፍል ነው፡፡ ይህ ረዘም ያለ ክፍል የደብዳቤውን ዋና ክፍል ይዟል፡፡ የጳውሎስ *መመሪያዎች* በሦስት ይከፈላሉ፡፡ አንደኛ፣ በ2፡1-17 ውስጥ፣ ጳውሎስ ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ *መመሪያ* ይሰጣቸዋል፡፡ ወደ ኋላ ላይ በዚሁ ትምህርት እነዚህን ጥቅሶች በጥንቃቄ እንቃኛቸዋለን፣ አሁን የምናደርገው ክርስቶስ ተመልሷል ሚለውን ሃሳብ ጳውሎስ አለመቀበሉን ብቻ እናያለን፡፡ በ2፡3 እንዲህ አስቀምጦታል፡

> ***ማንም በማናቸውም መንገድ አያስታችሁ፤ ከህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና። (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡3)***

በመቀጠል ደግሞ፣ በ3፡1-5፣ ስለ እርሱና አብረውት ስለባልደረቦቹ የአገልግሎት ስኬትና ደህንነት እንዲጸልዩላቸው ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች ይጠይቃል፡፡ ሦስተኛ፣ በ3፡6-15 ውስጥ፣ ጳውሎስ የተሰሎንቄን ሰዎች ወደ ሥራቸው እንዲመለሱና ለራሳቸው የሚያስፈልጋቸውን እንዲያዘጋጁ በመንገር፣ ስለታየባቸው ሃላፊነት የጎደለው አኗኗር ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ በ3፡10 እንዳስቀመጠው፡

> ***ደግሞ ከእናንተ ጋር ፡-ሊሠራ የማይወድ አይብላ ብለን አዘናችሁ ነበርና። (2ኛ ተሰሎንቄ 3፡10)***

እንደተመለከትነው፣ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፋቸው ሁለት አጫጭር ደብዳዎች በብዙ መንገዶች ይመሳሰላሉ፡፡ ሁለቱም ስለ ቤተክርስቲያኒቱ የሚሰማውን ደስታና እርሱ በሌለበት ስላሳት ታማኝነት ያለውን አድናቆት ይገልጻሉ፡፡ ሆኖም፣ እርሱ በሌለበት ወቅት ብርቱ ችግር በመካከላቸው እየተፈጠረ እንደሆነም ጳውሎስ ያውቃል፣ ስለዚህ እነዚህን ሁለት መልእክቶች በመጻፍ አንድ ጊዜ ብቻ ሳይሆን ሁለት ጊዜያት ለተሰሎንቄ ሰዎች መመሪያ ይሰጣቸዋል፡፡ ወነኛው ፍላጎቱ ለክርስቶስና ለትምህርቶቹ ታማኝ እንዲሆኑ፣ በእለት ከዕለት ሕይወታቸውም ሃላፊነት በሚሰማው መንገድ እንዲመላለሱ ደግሞም ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ትክክለኛውን ግንዛቤ እንዲጨብጡ ነበር፡፡

እስከዚህ ነጥብ ድረስ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን የጻፋቸውን መልእክቶች ዳራና የመልእክቶቹን መሠረታዊ ይዘቶች ተመልክተናል፡፡ አሁን ደግሞ ሦስተኛውን ርእሳችንን መመልከት የምንችልበት ስፍራ ላይ ደርሰናል፡፡ እነዚህ ደብዳቤዎች የጳውሎስን የነገረ-ፍፃሜ (የመጨረሻው ዘመን) አስተምህሮ ማእከላዊ ሃሳብ እንዴት እንደሚያንጸባርቁ እንመለከታለን፡፡

# 4. ነገረ-መለኮታዊ አመለካከት

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤው ውስጥ፣ ከሕይወታቸው ጋር የተያያዙ አንዳንድ ጉዳዮችን አንስቷል፡፡ ስለ ሐሰተኛ ነቢያት ጽፏል፣ ስለ ማመንና ሃላፊነት ስለሚሰማው አኗኗር እና ስለ ክርስቶስ ዳግመኛ

መመለስ ያላቸውን የተዛነፈ አመለካከት አርሟል፡፡ ሆኖም ቀደም ባሉት ትምህርቶች እንደተመለከትነው፣ ጳውሎስ በእነዚህ ደብዳቤዎች ውስጥ መሠረታዊ በሆነ መንገድ ያካተታቸውን ትምህርቶች ማለትም ያስተማራቸውን ነገሮች በሙሉ ስብስብ አድርገው የሚዙለትንና ያሰመረባቸውን ነገረ-መለኮታዊ ቁርጠኛ አቋሞች ለይቶ መመልከቱ ይጠቅማል፡፡ በሌሎቹ መልእክቶች እንዳየነው፣ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፈውም መልእክት የመነጨው ከነገረ-መለኮቱ ማእከላዊ ሃሳብ፣ ማለትም ከነገረ-ፍጻሜው ውስጥ ነው፡፡
የጳውሎስ ነገረ-ፍፃሜ የተገኘው እግዚአብሔር ታሪክን ከቀነበበት ከብሉይ ኪዳኑ አመለካከት እንደሆነ በቀላሉ መገንዘብ ትችላላችሁ፡፡ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን ይኖሩ የነበሩ አብዛኞቹ አይሁዶች ታሪክ በሁለት ዘመናት ማለትም፣ "የአሁን ዘመን" እና "የሚመጣው ዘመን" ተብሎ እንደሚከፈል ያምናሉ፡፡ የአሁን ዘመን ማለት አሁን ያለንበትን የኃጢአት፣ የፍርድ እና ሞት ዘመን የሚያመለክት ቃል ነው፡፡ "የሚመጣው ዘመን" ግን በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ የሚሆነውን የመጨረሻ ፍርድ እና ለእግዚአብሔር ህዝብ የሚመጣውን በረከት የሚያሳይ ዘመን ነው፡፡ በዚህ አመለካከት መሰረት፣ የመሲሁ ወይም የክርስቶስ መምጣት ለእነዚህ ለሁለቱ ዘመናት የሽግግር ወቅት ነው፡፡ መሲሁ ሲመጣ፣ የዚህን ዘመን ፍፃሜ ያመጣል የመጪውንም ዘመን አስደናቂ ነገሮች ያስተዋውቃል፡፡

እንግዲህ፣ እንደ ክርስቶስ ተከታዮች፣ ጳውሎስና የተቀሩት ሐዋርያት ይህንን ቀጥተኛ የሆነ ባለሁለት ክፍል የታሪክ ክፍፍል አመለካከት አጣጥመው አቅርበውታል፡፡ ኢየሱስ መሲህ እንደሆነ ደግሞም ኢየሱስ መጪውን ዘመን እንዳበሰረም ያውቃሉ፡፡ ሆኖም ደግሞ መጪው ዘመን ገና ወደ ሙላቱ እንዳልደረሰ እና ይህም ዘመን እንዳላበቃም ያውቃሉ፡፡ ስለዚህ፣ የክርስቶስ ተከታዮች "የሆነና" "የሚሆን" ብለው በሚጠሩት አስተሳሰብ ማለትም የዘላለም ድት ያገኘንበት ዘመን በአንዳንደ መንገዶች አሁን እዚህ "ሆኗል" ግን "ገና" ወደ ሙላቱ አልደረሰም፡፡

ይህ የነገረ-ፍፃሜ ንድፍ በመጀመሪያዪቱ ቤተክርስቲያን ላይ ከባድ ችግር ፈጥሮባታል ምክንያቱም፡ ከሚመጣው ዘመን ምን ያህሉ ነው አሁን እዚህ የተፈጸመው? የሚል ጥያቄ ስለሚያስነሳ ነው፡፡ አንዳንዶችም እንደ ክርስቲያንነታቸው ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት በሚያደርጉት ጥረት ወደ አንድ ጽንፍ አጋድለው ይገኛሉ፡፡ ጳውሎስና የገላትያ ሰዎች በተሰኘው ትምህርታችን እንዳየነው፣ አንዳንድ ክርስቲያኖች ክርስቶስ በመጀመሪያ መምጣቱ ላከናወናቸው ነገሮች ዝቅተኛ ግምት በመስጠት፣ የሚመጣው ዘመን ገና ወሳኝ በሆነ መልኩ አልመጣም የሚል አቋም ነበራቸው፡፡ ይህን ሚዛኑን ያልጠበቀ አመለካከት "ነገረ-ፍፃሜን ያለመገንዘብ አስተሳሰብ" ብለን ሰይመነዋል፡፡

በተሎንቄም፣ ደግሞ፣ ሌላኛው ጽንፍ ተገልጦ ይታያል፡፡ የተሰሎንቄ ሰዎች "ያለ ልክ የጋለ የነገረ-ፍፃሜ አስተሳሰብ" አዳብረው ነበር፡፡ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች፣ በሐሰተኛ ነቢያቱ ተፅዕኖ ምክንያት፣ የመጪው ዘመን ሙላት ተፈፅሟል ወይም በቅርቡ ይሆናል ብለው አምነው ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት፣ በዚህ ዘመን ከሕይወት ጋር የተያዙ በርካታ ጉዳዮችን እንደ ምናምንቴ ይቆጥሩ ነበር፡፡

ጳውሎስም ይህ "ይህ ያለ ልክ የጋለ ነገረ-ፍፃሜ" የተሰሎንቄን ሰዎች ወደ ከባድ ችግር ውስጥ እንደከተታቸው ተገንዝቧል፡፡ ስለዚህ፣ በዚህ ዘመንና በመቺው ዘመን መካከል ያለውን የሽግግር ወቅት ሚዛኑን በጠበቀ መንገድ እንዲገነዘቡ ለማድረግ ጽፎላቸዋል፡፡

ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች ለገቡበት ችግር ምላሽ የሰጠው ስለ መጨረሻው ዘመን ያላቸውን አመለካከት ሚዛን በማስጠበቅ ነው፡፡ ይህንንም በሦስት ወሳኝ መንገዶች አከናውኖታል፡፡ አንደኛ፣ ትምህርት ድነትን የተሰሎንቄን ሰዎች ነገረ-ፍፃሜ ሚዛን በሚያስጠብቅ መንገድ አብራርቶላቸዋል፡፡ ሁለተኛ፣ ጳውሎስ ስለ መጨረሻው ዘመን ያለውን ግንዛቤ ከክርስቲያናዊ ግብረገብነትና ሥነ-ምግባር ጋር አዛምዶላቸዋል፡፡ ሦስተኛ ደግሞ፣ ከክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ አስቀድመው ከሚከናወኑ ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ የተሰሎንቄ ሰዎች ያሉበትን ስፍራ አሳይቷቸዋል፡፡ የጳውሎስ ትምህርተ ድነት የተሰሎንቄን ሰዎች ነገረ-ፍፃሜ ሚዛን የሚያስጠብቅባቸውን መንገዶች አስቀድመን እንመልከት፡፡

# ትምህርተ ድነት

ጳውሎስ ያለ ልክ የጋለውን የተሰሎንቄ ሰዎች ነገረ-ፍፃሜ ቀዝቀዝ ለማድረግ የተጠቀመው ስልት፣ ቸል ያሉትንና በክርስቶስ ያገኙትን ድነት ስፋትና ጥልቀት ማሳሰብን ነው፡፡ በሐሰት ነቢያቱ ተፅዕ ምክንያት፣ በርካታ የተሰሎንቄ ሰዎች ድነትን አገናኝተው የነበረው በክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ከሚያገኟቸው በረከቶች ጋር ነበር፡፡ በክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ከሚገኝ በረከት በስተቀር ሌላው ሁሉ ምንም ፋይዳ የለውም የሚል ድምዳሜ ነበራቸው፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ ይህንን ከልክ ያለፈ የወደፊት አፅንኦት ለማፈራረስ፣ ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመለስ የሚገኘው ድነት የሚመሠረተው አሁን በተከናወነው ማዳን ረገድ መሆኑን ያመለክታል፡፡ የተሰሎንቄ ሰዎች እንዲኖራቸው የሚፈልገውን አመለካከት አስመልክቶ ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13-14 እጅግ ጠቃሚ ሃሳብ አስፍሯል፡፡

> ***እኛ ግን፥ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት መርጦአችኋልና፤***
> ***ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ።***
> ***(2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13-14)***

ስለነዚህ ጥቅሶች ብዙ ሊባል ይችላል፣ ሆኖም በዚህ ስፍራ ስለተጠቀሱ ሦስት የድነት ገጽታዎች ጥቂት ማለት እንወዳለን፡፡ አስቀድመንም ጳውሎስ ትኩረታቸውን ወዳለፈው ድነት እንዴት እንደሳበው እናያለን፣ ከዚያም ትኩረታችንን ስለ ወደፊቱ ድነታቸውም ምን ያህል እንደሚስብ ወደማየቱ እናዞራለን በመጨረሻም፣ ይህ ምንባብ የአሁኑን ወይም ወቅታዊውን የድነት ገጽታ እንዴት እንደሚነካው እንረምራለን፡፡ በመጀመሪያ ጳውሎስ ያለፈውን ድነት እንዴት እንደገለጸው እንመልከት፡፡

## የተፈጸመ ድነት

ያለፈውን የድነት ገጽታ አስመልክቶ፣ ጳውሎስ የሚናገረው እግዚአብሔር የተሰሎንቄን ሰዎች ስለመረጠበት ምርጫ ነው፡፡ እግዚአብሔር የተሰሎንቄን ሰዎች መርጧቸዋል ይላል ጳውሎስ፣ ማለትም የተሰሎንቄ ሰዎች በጳውሎስ የወንጌል ስብከት ወደ እምነት ከመምጣታቸውም አስቀድሞ የተሰሎንቄን ሰዎች ወደዳቸው ስለዚህም ሊያድናቸው ወሰነ ማለት ነው፡፡ ይህ ምርጫ እንዲያውም እግዚአብሔር ዓለምን ከመፍጠሩ አስቀድሞ ተከናወነ፡፡ በኤፌሶን 1፡4 ውስጥ እግዚአብሔር እንዴት ሰዎችን እንደመረጠ ጳውሎስ የተናገረውን እናድምጥ፡

> ***ዓለም ሳይፈጠር፥ በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን።***
> ***(ኤፌሶን 1፡4)***

ይህ ሃሳብ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13 ውስጥም የተንጸባረቀ ይመስላል፡፡ ጳውሎስ እንዲህ ጽፏል፡

> ***እኛ ግን፥ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት መርጦአችኋልና፤ (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13)***

የጳውሎስ ነጥብ ግልጽ ነው፡ የተሰሎንቄ ሰዎች የዳኑት እግዚአብሔር ለድነት ስለመረጣቸው ነው፡፡ ድነት የተመሠረተው ሰዎች በየታሪክ ዘመናቱ ባካሄዷቸው ምርጫዎች ሳይሆን በእግዚአብሔር የዘላለም ፈቃድ ነው፡፡

እንግዲህ በጳውሎስ አስተሳሰብ፣ ምርጫ እርስ በርሱ ተያዥነት የሌለው፣ ወይም መልኩን እየቀያየረ የተከናወነ ድርጊት አይደለም፡፡ በኤፌሶን 1፡4 እንዳየነው፣ የእግዚአብሔር ምርጫ "በክርስቶስ" ተፈጽሟል፡፡ በሌሎቹ ትምህርቶች እንዳየነው ደግሞ፣ በክርስቶስ መሆን ማለት ከኢየሱስ ጋር አንድ መሆን ማለት ሲሆን፣ እርሱ በሞቱና በትንሣኤወ ከዚህ ዘመን ወደ መጪው ዘመን እንደተሻገረ ሁሉ፣ እኛም ከእርሱ ጋር በመተባበራችን፣ ከዚህ ዘመን ወደ መጪው ዘመን ተሸጋግረናል፡፡ ስለዚህ ጳውሎስ፣ የተሰሎንቄን ሰዎች ስለመመረጣቸው ሲያሳስባቸው፣ በልቡናው ያለው ከኢየሱስ ጋር አንድ እንዲሆኑና ከእርሱም ጋር ከዚህ ዘመን ወደ መጪው ዘመን እንዲሸጋገሩ እግዚአብሔር እንደመረጣቸው ነው፡፡
ጳውሎስ በተጨማሪም፣ ስለ ተሰሎንቄ ሰዎች ድነት ሌላኛው ገፅታ፣ ማለትም ስለ መለወጣቸው የጻፈው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡14 ውስጥ "እግዚአብሔር እናንተን ለዚህ በወንጌላችን ጠራችሁ" ያለውን ልብ በሉ፡፡ ጳውሎስ "በወንጌሉ አማካይነት" የተሰሎንቄን ሰዎች ወደ ድነት "ጠራቸው፡፡" ጳውሎስ በዚህ ስፍራ የሚጠቅሰው በሁለተኛው ሚሲዮናዊ ጉዞው ለተሰሎንቄ ሰዎች የክርስቶስን ወንጌል የሰበከላቸው መሆኑን ነው፡፡ የክርስቶስን የምሥራች ወንጌል ሰሙና አመኑ፣ በዚህም ለወንጌል በሰጡት የመጀመሪያ ምላሽ ድነትን አገኙ፡፡

በ1ኛ ተሰሎንቄ 1፡4-5፣ ድነት በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ምርጫ ደግሞም የተሰሎንቄ ሰዎች ባመኑ ወቅት እንደተገኘ ይናገራል፡፡

> ***በእግዚአብሔር የምትወደዱ ወንድሞች ሆይ፥ እንደ ተመረጣችሁ አውቀናልና።***
> ***ወንጌላችን በኃይልና በመንፈስ ቅዱስ በብዙ መረዳትም እንጂ በቃል ብቻ ወደ እናንተ አልመጣምና፤ በእናንተ ዘንድ ስለ እናንተ እንዴት እንደ ነበርን ታውቃላችሁ።***
> ***(1ኛ ተሰሎንቄ 1፡4-5)***

የተሰሎንቄ ሰዎች መለወጥ እግዚአብሔር አስቀድሞውኑ እንደመረጣቸው አረጋግጧል፡፡ ጳውሎስ ይህንን በተሰሎንቄ ሰዎች ሕይወት የታየና የተፈጸመ ድነት ገፅታ በማመልከት፣ ለእነርሱ የሰበከላቸውን ወንጌል ያረጋግጣል፣ ደግሞም የድነትን የተወሰነ ክፍል እየተለማመዱት እንደሆነም ማረጋገጫ ይሰጣቸዋል፡፡

## የወደፊት ድነት

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ በድነት ላይ አትኩሮት ያደረገበት ሁለተኛው መንገድ ስለ መዳናቸው የወደፊት ገጽታ እንዲያስቡ ማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ፣ በ1ኛ ተሰሎንቄ 1፡10 ጳውሎስ ስለ አማኞች እንዲህ ይጽፋል፡

> ***ለሕያውና ለእውነተኛ አምላክም ታገለግሉ ዘንድ፥ ከሙታንም ያስነሳውን ልጁን እርሱንም ኢየሱስን ከሚመጣው ቍጣ የሚያድነንን ከሰማይ ትጠብቁ ዘንድ፥ (1ኛ ተሰሎንቄ 1፡10)***

በተመሳሳይም መንገድ፣ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡14 ውስጥ፣ የመለኮታዊ ቤዝዎት የመጨረሻ ግቡ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት እንደሆነ አመልክቷል፡፡

የተሰሎንቄ ሰዎች በክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ጉዳይ ከልክ በላይ መጨነቃቸው ልክ ባይሆንም፣ የክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ድነትን ወደ ፍፃሜ እንደሚያመጣው ጳውሎስ እውቅና ሰጥቷል፡፡ የተሰሎንቄ ሰዎች ሁሉንም በአግባቡ ሲረዱ፣ የድነት የመጨረሻው ግቡ ከመለኮታዊ ቁጣ ነፃ መውጣትና የክርስቶስ ተከታዮች መክበር ነው፡፡ ወደፊት በአዲስ ሰማይና በአዲስ ምድር ከክርስቶስ ጋር ስንነግሥ ፍፁም ተለውጠን ሊገመት በማይቻል ክብር እንደምንከብር መቀበል ጳውሎስን አያስፈራውም፡፡

## የአሁን ድነት

በሦስተኛ ደረጃ፣ የድነትን ያለፈና የወደፊት ገጽታ ከመጥቀሱ በተጨማሪ፣ ጳውሎስ ስለ ድነት በተግባር እየተገለጠ ያለ የአሁን ጊዜ ገጽታ ይናገራል፡፡ ይህንን የድነት ገጽታ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13 ውስጥ በሁለት መንገዶች ይጠቅሰዋል፡፡

> ***እኛ ግን፥ በጌታ የተወደዳችሁ ወንድሞች ሆይ፥ ሁልጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን ልናመሰግን ግድ አለብን፥ እግዚአብሔር በመንፈስ መቀደስ እውነትንም በማመን ለመዳን እንደ በኵራት መርጦአችኋልና፤ (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13)***

በአንድ በኩል፣ የተሰሎንቄ ሰዎች ድነትን ያገኙት "በመንፈስ በመቀደስ" እንደሆነ ጳውሎስ ያመለክታል፡፡ በሌሎቹ ትምህርቶች እንዳየነው፣ መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር ህዝብ ላይ በትልቅ ሁኔታ የፈሰሰው ክርስቶስ ወደ ላይ ሲያርግ ነበር፡፡ ይህም የመጪው ዘመን በረከት እንደሆነ ጳውሎስ ያመለክታል፡፡ እንዲያውም፣ በኤፌሶን 1፡14 ውስጥ፣ መንፈስ ቅዱስ በሚመጣው ዘመን የምንቀቀበለው ውርስ "ቀብዱ/መያዣ" እንደሆነ ይገልጸዋል፡፡ ስለዚህ፣ ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ በተሰሎንቄ ሰዎች ሕይወት ውስጥ እየሠራ እንደሆነ ሲጠቅስ፣ ትኩረታቸውን ሊስብ የሚፈልገው ወደ ፊት በትልቅ ጉጉት የሚጠባበቁትን ታላቅ ርስት አሁን በዚህ እየተለማመዱት እንደሆነ ነው፡፡

የአሁን ዘመንና መጪው ዘመን አብረው በሚጓዙበት በዚህ ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት እጅግ ወሳኝነት አለው፡፡ በዚህ የኃጢአትና የሞት ዘመን ያለው የተበለሻሸ ሥርዓት በማያቋርጥ ሁኔታ አማኞችን ማጥፋትን ይናፍቃል፡፡ ሆኖም የሚመጣው ዘመን ቀብዱ የሆነው መንፈስ ቅዱስ፣ እኛን  ዘወትር በማንፃት ከዓለም ርኩሰት ይለየናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ፣ ጳውሎስ የአሁኑን ዘመን ድነት የሚያመለክተው እኛ የዳንነው "እውነቱን በማመን" እንደሆነ በመጥቀስ ነው፡፡ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡13 ውስጥ፣ በዚህ ስፍራ እርሱ የሰበከላቸውን የእውነት ቃል በመውደድና ከሐሰተኛ ነቢያት ራሳቸውን በመጠበቅ ለእግዚአብሔርና ለክርስትና እምነት ያላቸውን ታማኝነት አጥብቀው እንዲይዙ የተሰሎንቄን ሰዎች በማበረታታት፣ አማኞች ስላለባቸው ሃላፊነት ይናገራል፡፡  ክርስቶስ አሁን በሕይወታቸው እየሠራ ስላለው የማዳን ሥራ እውነትን በማመን መዝለቃቸው እጅግ ወሳኝ መሆኑን በጽኑ ያመለክታል፡፡

ልክ እንደ ተሰሎንቄ ሰዎች ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ዳግመኛ መመለስ ላይ ከልክ ባለፈ መንገድ ትኩረት በማድረግ ከዚያም የተነሳ ካለፈውና አሁንም ካለው መዳናቸው የተገኘውን እድልና ሃላፊነት የዘነጉ በርካታ የክርስቲያኖች ቡድኖች እንደነበሩ በቤተክርስቲያን ታሪክ ውስጥ እናገኘለን፡፡ ምንም እንኳን ክርስቶስ በክብር ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ በጉጉት መጠበቅን ችላ ማለት ባይገባንም፣ እግዚአብሔር ለእኛ እስካሁን ምን ያህል እንዳደረገልንና አሁንም እያደረገልን እንዳለ ዘወትር ልናስታውስ ይገባናል፡፡

# ግብረ-ገባዊነት

ጳውሎስ በተሰሎንቄ የነበረውን ያለ ልክ የጋለ ነገረ-ፍፃሜ የተጋፈጠው ባለፈውና በአሁኑ ድነት ገጽታ ላይ በማተኮር ብቻ ሳይሆን፣ በክርስቲያናዊ የአኗኗር ሥነ-ምግባርም ላይ ከፍተኛ አፅንዖት በመስጠትም ጭምር ነበር፡፡ የሥነ-ምግባር አስተምህሮው ነገረ-ፍፃሜውን ምን ያህል እንዳንጸባረቀለት ለመመልከት፣ ሁለት ርዕሶችን እንዳስሳለን፡፡ እነርሱም፣ የድነት ሂደትና በሥነ-ምግባር የታነፀ አኗኗር አንድምታ ናቸው፡፡ አስቀድመን የጳውሎስ ነገረ-ፍፃሜ ያለፈውና የአሁን መዳን ገጽታ ለወደፊቱ በረከት እንዴት አድርጎ እንደሚዘጋጀን የገለጸበትን መንገድ እንመልከት፡፡

## የድነት ሂደት

ጳውሎስ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡14 የተሟላውን የድነት ሂደት ምስል ገልጦ አሳይቷል፡፡

> *ለዚህም የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለማግኘት በወንጌላችን ጠራችሁ። (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡14)*

የተሰሎንቄ ሰዎች የተቀደሱትና እውነትን ያመኑት “የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ክብር ለመቀበል” እንደሆነ ጳውሎስ ይጽፋል፡፡ በ1ኛ ተሰሎንቄ 3፡13 ውስጥም ጳውሎስ በጸለየው ጸሎትተመሳሳይ ሃሳብ ገልጧል፡፡

> *ጌታችንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ሁሉ ጋር ሲመጣ፥ በአምላካችንና በአባታችን ፊት በቅድስና ነቀፋ የሌለበት አድርጎ ልባችሁን ያጸና ዘንድ፥ እኛ ደግሞ ለእናንተ እንደምንሆን ጌታ እርስ በእርሳችሁ ያላችሁን ለሁሉም የሚሆን ፍቅራችሁን ያብዛ ይጨምርም። (1ኛ ተሰሎንቄ 3፡12-13)*

ክርስቶስ ከቅዱሳኑ ጋር ተመልሶ የሚመጣበትን ጊዜ የተሰሎንቄ ሰዎች ይጠባበቃሉ፣ ጳውሎስም ያንን ናፍቆት እውቅና ይሰጠዋል፡፡ ሆኖም በዕለት ከዕለት ኑሯቸው ለክርስቶስ ታማኝ ሆነው እንዲዘልቁ፣ ክርስቶስም ዳግመኛ ሲመለስ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች በፊቱ ያለ እፍረት ለመገኘት እንዲበረቱም ጳውሎስ ይጸልይላቸዋል፡፡ በዘላለማዊ ክብር የሚገለጠው የወደፊት ድነት የሂደቱ ድምዳሜ ወይም ግብ ነው፡፡ እግዚአብሔር ያለፈውንና የአሁን ድነታችንን ልምምድ ያቀደው ወደፊት ወደሚመጣው ድነታችን የሚመራን እንዲሆን አድርጎ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ያለፈውና የአሁን ድነት ሳይኖር፣ ወደ ፊት ወደሚጠበቀው መዳን አይደረስም፡፡

## ሥነ-ምግባራዊ አንድምታ

ጳውሎስ ያለፈውን፣ የአሁኑንና የወደፊቱን የድነት ገፅታ ሲገልፅ፣ በዚያ ሂደት ውስጥ የሚከናወን አንድ ወሳኝ እርምጃ ዕለት በዕለት የምንመላለስበት ስነ-ምግባራዊ አኗኗር መሆኑን ያመለክታል፡፡ በአጭሩ፣ አማኞች ነን ብለው እያወጁ በጽድቅ መመላለስ ያልቻሉ ሰዎች ሂደቱን ሊያጠናቅቁ አይችሉም፣ ምክንያቱም በትክክለኛ መንገድ ገና አልጀመሩትምና ነው፡፡ ጳውሎስም ይህንን ነጥብ ረገጥ በማድረግ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች ክርስቶስ ዳግመኛ ሲመጣ የሚያገኟቸውን በረከቶች ተስፋ ማድረጋቸው ትክክል ቢሆንም፣ እነዚህን በረከቶች ለመቀበል በእውነት ተስፋ የሚያደርጉ ከሆነ፣ አሁን በዚህ ዘመን እየኖሩ ባሉበት ሕይወት በብርቱ መትጋት እንዳለባቸውም ያሳስባቸዋል፡፡

አንግዲህ አሁን ይህን ስንል፣ ከሌሎች ምንባቦች መረዳት እንደምንችለው በክርስቶስ በእውነት ያመኑ አማኞች ድነታቸውን ያጣሉ ብሎ ጳውሎስ እንደማያምን እርግጠኛ ነን፡፡ ለምሳሌ፣ በፊልጵስዩስ 1፡6 ውስጥ ጳውሎስ የፊልጵስዩስን ሰዎች እንዲህ በማለት ማረጋገጫ ይሰጣቸዋል፡

> *በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እስከ ኢየሱስ ክርስቶስ ቀን ድረስ እንዲፈጽመው ይህን ተረድቼአለሁና፤ (ፊልጵስዩስ 1፡6)*

ግን፣ በ1ኛ ተሰሎንቄ 5፡5-9 ጳውሎስ በእንዴት ያለ መንገድ እንደሚያሳስባቸው እናዳምጥ፡

> *ሁላችሁ የብርሃን ልጆች የቀንም ልጆች ናችሁና። እኛ ከሌሊት ወይም ከጨለማ አይደለንም፤*
> *እንግዲያስ እንንቃ በመጠንም እንኑር እንጂ እንደ ሌሎች አናንቀላፋ።*

*የሚያንቀላፉ በሌሊት ያንቀላፋሉና፥ የሚሰክሩም በሌሊት ይሰክራሉና፤*
*እኛ ግን ከቀን ስለ ሆንን፥ የእምነትንና የፍቅርን ጥሩር የመዳንንም ተስፋ እንደ ራስ ቁር እየለበስን በመጠን እንኑር፤*
*እግዚአብሔር ለቍጣ አልመረጠንምና፥ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ መዳንን ለማግኘት ነው እንጂ። (1ኛ ተሰሎንቄ 5፡5-9)*

ጳውሎስ ስለ ድነት ያለው ባለሦስትዮሽ የድነት አተያይ በዚህም ምንባብ ተገልጾአል፡፡ ባለፈው ጊዜ፣ የተሰሎንቄ ሰዎች "የብርሃንና የቀን ልጆች" ሆነዋል፡፡ በእግዚአብሔር አይን አሁን እነርሱ ይህንን ልዩ ደረጃ ተቀብለዋል፡፡ ስለዚህም በመዳናቸው ታማኞች፣ አፍቃሪዎችና ባለተስፋዎች ሆነዋል፡፡ ያለፈውን መዳን በመቀበላቸው ምክንያት፣ በአሁን ዘመንም በመዳናቸው የመዝለቅ ግዴታ እንዳለባቸው ሲያሳስባቸው፣ "እንንቃ በመጠንም እንኑር" ይላቸዋል፡፡ ከዚህም ባሻገር፣ ክርስቲያኖች በመጠን መኖር፣ መንቃት፣ በእምነት መጽናት፣ በተስፋ እና በፍቅር መኖር ለምን እንደሚገባቸው ሲገልጽ፣ የወደፊቱ መዳናችን ከእነዚያ ጋር ግንኙነት ስላላቸው እንደሆነ ያብራራል፡፡ እግዚአብሔር በቁጣው እንድንቃጠል ሳይሆን፣ የጠራን ለድነት ነው፡፡ ሆኖም ደግሞ የወደፊቱን ድነታችንን ለመቀበል በአሁኑ ሕይወታችን በታማኝነት እንድንዘልቅም ጠርቶናል፡፡

በዚህ መሠረት፣ ጳውሎስ በ1ኛ እና በ2ኛ ተሰሎንቄ መልእክቶች በርካታ ግብረገባዊ መመሪያዎችን አካቷል፡፡ ለምሳሌ፣ በ1ኛ ተሰሎንቄ 4፡3-5፡22 እንዳየነው፣ ራሳቸውን የሚያስችላቸውን ሥራ እንዲሠሩ፣ ከአመንዝራነት እንዲርቁ፣ እርስ በርስ እንዲዋደዱና እንዲበረታቱ፣ ክፉውን በመልካም እንዲያሸንፉ እና የተቀደሰ ሕይወት እንዲኖሩ አሳስቧቸዋል፡፡

ለተሰሎንቄ ሰዎች የተሰጡት እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉት ለየት ያሉ መመሪያዎች የመነጩት ክርስቲያኖች አሁን እየኖሩበት ባሉት ገሃዳዊ የድነት እውነታ ውስጥ ሊመላለሱባቸው ይገባል ከሚለው የጳውሎስ ቁርጠኛ ሃሳብ ነው፡፡ የጳውሎስ ነገረ-ፍፃሜ ካለፈውና ከአሁኑ የድነት ገጽታ ወደመጪው መዳን የምንሸጋገርበትን ሂደትም ያካትታል፡፡

## ታሪካዊ ስፍራ

ጳውሎስ የተሰሎንቄ ሰዎች ይዘውት የነበረውን እጅግ የጋለ ነገረ-ፍፃሜ ለማረም የተጠቀመበት ሦስተኛ መንገድ ከክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ በፊት ከሚከናወኑ ተግባራት ጋር በተገናኘ መንገድ የሚኖራቸውን ታሪካዊ ስፍራ ማሳየት ነው፡፡ እንደምታስታውሱት በርካታ የተሰሎንቄ አማኞች ከጌታ መመለስ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳዮች ረገድ ግራ ተጋብተው ነበር፡፡ አንዳንዶቹ እንዲውም ክርስቶስ ተመልሷል ብለው ተታልለው ስለነበር መመለሱ እንዳመለጣቸው ያስቡ ነበር፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ክርስቶስ እስካሁን በይመጣም፣ በጣም በቅርቡ ይመጣል ብለው ያምኑ ነበር፡፡

ጳውሎስ ለእነዚህ የተሳሳቱ ሃሳቦች ምላሽ የሰጠው ከክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ አስቀድመው ስለሚከናወኑ ጉዳዮች የተሰሎንቄን ሰዎች በማሳሰብ ነው፡፡ የሚላቸውም እነዚህ ነገሮች ገና ወደ ብርሃን ይመጣሉ/ይገለጣሉ ነበር፡፡ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-8 የጻፈውን አድምጡ፡

*ነገር ግን፥ ወንድሞች ሆይ፥ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ...*
*... ክህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ፥ አይደርስምና። ...*

*ገና ከእናንተ ጋር ሳለሁ፥ ይህን እንዳልኋችሁ ትዝ አይላችሁምን?*
*በገዛ ራሱ ጊዜም ይገለጥ ዘንድ፥ የሚከለክለውን አሁን ታውቃላችሁ።*

*የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራልና፤ ብቻ ከመንገድ እስኪወገድ ድረስ አሁን የሚከለክል አለ። በዚያም ጊዜ ጌታ ኢየሱስ በአፉ መንፈስ የሚያጠፋው፥ ሲመጣም በመገለጡ የሚሽረው ዓመፀኛ ይገለጣል፤ (2ኛ ተሰሎንቄ 2፡1-8)*

ይህ ምንባብ ገና ከቤተክርስቲያን የመጀመሪያ ዓመታት አንስቶ እጅግ አስገራሚ ተርጓሚዎች የነበሩት ሲሆን ትክክለኛው ፍቺው ምንድነው ከሚለው አንፃር ግን የተለያዩ አመለካከቶች አሉ፡፡ በጥቅል አነጋገር፣ የተሰሎንቄ ሰዎች የነበራቸው ያለ ልክ የጋለ ነገረ-ፍፃሜ መስመሩን የሳተ ስለሆነ ክርስቶስ በክብር ከመምጣቱ አስቀድሞ አንዳንድ ክንዋኔዎች ሊከናወኑ ይገባል በማለት ጳውሎስ አስተምሯቸዋል ማለት እንችላለን፡፡ እንደዚህ ምንባብ አገላለጽ፣ ክርስቶስ ከመመለሱ አስቀድሞ ቢያንስ አራት ነገሮች ሊፈጸሙ ይገባል፡ የዓመፅ ምሥጢር ሊሠራ ይገባል ግን ይከለከላል፤ ጥፋት ወይም ክህደት ሊገለጥ ይገባዋል፤ ከልካዩ ሊወገድ ይገባዋል ደግሞም የዓመፅ ሰው ሊገለጥ ይገባዋል፡፡

እነዚህን አራት ክንውኖች ተርጓሚዎች በተለያዩ መንገዶች ይገነዘቧቸዋል፣ ስለዚህ በዚህ ነጥብ ላይ ሁሉን ሰው ሊያረካ በሚችል  መጠን እያንዳንዱን ጉዳይ መዳሰስ አንችልም፡፡ ስለዚህ፣ በዚህ ነጥብ ላይ በሰፊው ተቀባይነት ያላቸውንና ለእኛም አሳማኝ የሆኑትን ጥቂት አመለካከቶች እናቀርባለን፡፡

በመጀመሪያ፣ ጳውሎስ "የዓመፅ ምሥጢር አሁን ይሠራል" ደግሞም ከልካይ አለበት ብሎ ገልጧል፡፡ ሆኖም ይህንን ምሥጢርም ሆነ ከልካዩን በቀጥታ አልገለጠልንም፡፡ ሆኖም፣ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡7-9፣ ጳውሎስ ይህንን ምሥጢር በግልጽ ከቤተክርስቲያን ቀንደኛ ጠላት ከሰይጣን ጋር አገናኝቶታል፡፡ ስለዚህ ይህ ምሥጢር በተፈጥሮው አጋንንታዊ ለመሆኑ ፍንጭ ይሰጠናል፡፡ በተጨማሪም ጳውሎስ ቤተክርስቲያን ከምድር ገዢዎች ጋር ሳይሆን፣ ከመንፈሳውያን ኃይላት ጋር ውጊያ ላይ እንዳለችም እንደተቀሰ አስተውሉ፡፡ በኤፌሶን 6፡12 እንዲህ ጽፏል፡

*መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ። (ኤፌሶን 6፡12)*

አጋንንታዊ ኃይላት በምድር ላይ የሚተባበሯቸው ምድራዊ አጋሮች ማለትም ክፋትን የተሞሉ መንግሥታት እና ለክርስቶስ ጀርባቸውን የሰጡ ግለሰቦች ይጠቀሳሉ፡፡ ሆኖም ክርስቲያኖች አስቀድመው ከአጋንንታዊ እንቅስቃሴ አንፃር እንዲስቡት ደግሞም በምድር የሚካሄደው እንቅስቃሴ የመንፈሳዊው ጦርነት ቅጥያ እንደሆነ እንዲረዱ ያበረታታል፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ ጳውሎስ በደብዳቤዎቹ በጠቅላላ ከምሥጢሩና ከከልካይዋ ጋር ተዛማኝ የሆኑትን መንፈሳዊ ውጊያዎች በዝርዝር ደጋግሞ ይጠቅሳል፡፡ ለምሳሌ፣ በቆላስይስ 2፡15-20 እና በገላትያ 4፡8-9፣ የክርቶስ መሰቀል አማኞች ወደ እምነት ከመምጣታቸው አስቀድሞ በእነርሱ ላይ ይሰለጥኑ የነበሩትን አጋንንቶች "ትጥቃቸውን ያስፈታ" ሲሆን፣ መንፈስ ቅዱስም አማኞችን ከእነዚህ የሐሰት አማልክት ነፃ አውጥቷቸዋል በማለት አስተምሯል፡፡ በመሠረታዊነት፣ እነዚህ አጋንንታዊ ኃይላት አሁንም ይሠራሉ ሆኖም በእግዚአብሔር ጉልበት ተከልክለዋል፡፡

በእነዚህ ምክንያቶች፣ "የአመፅን ምሥጢር" መረዳት ያለብን በሰማያዊ ስፍራ ኃይልን የሚገልጥ፣ የእግዚአብሔር ተቃዋሚ፣ ለሐሰት መምህራንን ኃይል የሚሰጥ እና ሀሰተኛ ሃይማኖትን የሚያስፋፋ አጋንንታዊ ኃይል እንደሆነ ነው፡፡ በተዛዳኝ ደግሞ፣ "ከልካይ" ወይም "ገዳቢ" የተባለውን ልንረዳ የሚገባው በተቀዳሚነት በመንፈሳዊ

ዓለም ውስጥ ያሉ ፍጥረታት ምናልባትም መልአክ ወይም መላእክት ወይም መንፈስ ቅዱስ ራሱም ሊሆን እንደሚችል ነው፡፡

ሁለተኛ፣ ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች የሚያሳስባቸው “ክህደት” ወይም “ጥፋት” ሳይገለጥ ክርስቶስ አይመጣም የሚለውን ነው፡፡ ጳውሎስ በሚጽፍበት ዘመን ከልካዩ ስላለ፣ ክህደት ገና አልተፈፀመም፣ ስለዚህ ክርስቶስ አልተመለሰም ማለት ነው፡፡ ይህንን ክህደት ወይም ትፋት በጥሩ ሁኔታ የምንገነዘበው በራእይ መጽሐፍ ውስጥ ዮሐንስ ውጊያ ብሎ ከሚጠራው ጋር አቻ እንደሆነ ካሰብን ነው፡፡ በራእይ 16፡14፣ *“በታላቁም ሁሉን በሚገዛ በእግዚአብሔር ቀን ወደ ሚሆነው ጦር” ተብሏል፡፡* በራእይ 19፡19፣ *“በፈረሱም የተቀመጠውን ጭፍራዎቹንም ይወጉ ዘንድ” የተባለለት ነው፡፡ በራእይ 20፡8-9፣ ጦርነቱ፣ ‘የቅዱሳንንም ሰፈርና* የተወደደችውን ከተማ ከበቡ” የተባለለት ነው፡፡ ይህ ክህደት በመጨረሻው የጌታ ቀን በእግዚአብሔር ላይ የሚዘምቱትን የክፋት ኃይላት የሚያካትት ነው፡፡ ይህም እስከ መጨረሻው ቀን ድረስ አይገለጥም፡፡ በዚያን ጊዜም ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ በእርሱ ላይ የተነሱበትን ሁሉ ያጠፋቸዋል፡፡

ከዚህም ባሻገር፣ ከልካዩ የዓመፅን ምሥጢር መከልከሉን ሳያበቃ ክህደቱ እንደማይገለጥ ጳውሎስ ያመለክታል፡፡ የተሰሎንቄ ሰዎች ከልካዩ በትጋት እየሠራ መሆኑን ከተረዱ፣ ከክርስቶስ መምጣት ጋር እንተላለፋለን ከሚለው ፍርሃት ነፃ ይወጣሉ፡፡

በመጨረሻም፣ ጳውሎስ የሚገልፀው የዓመፅ ሰው ሳይገለጥ ክርስቶስ እንደማይመለስ ነው፡፡ በ2ኛ ተሰሎንቄ 2፡4-9 ጳውሎስ ከሰጠው መግለጫ እንደምንረዳው፣ ይህ የዓመፅ ሰው በስጋ የተገለጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን ተመስሎ ይገለጣል፡፡ ለምሳሌ በቁጥር 8 እንደ ኢየሱስ ይገለጣል ይላል፡፡ ቁጥር 6 ደግሞ በራሱ ጊዜ ይገለጣል ይላል፡፡ ቁጥር 9 ደግሞ የእርሱ መምጣት በተአምራት ሁሉና በምልክቶች በሐሰተኞች ድንቆችም እንደሚታጀብ ይናገራል፡፡ በቁጥር 4 ደግሞ እኔ አምላክ ነኝ ብሎ ያውጃል ይላል፡፡

የዓመፅን ሰው ማንነት አስመልክቶ በርካታ ሃሳቦች ሲሰነዘሩ ቆይተዋል፡፡ አንዳንዶቹ እውቅ የፖለቲካ ሰው ለምሳሌ፣ በመጀመሪያው ክፍለ ዘመን እንደነበረው እንደ ኖሩ ከላውዴዎስ ቄሳር ዓይነት ሰው አድርገው ያስቡታል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ በየዘመናቱ በተደጋጋሚነት እንደሚነሱት የፖለቲካ መሪዎች ዓይነት አድርገው ያስቡታል፡፡ ለምሳሌ፣ ምንም እንኳን ኔሮ የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን አሳዳጅ የነበረ ቢሆንም፣ እርሱን ተከትለው ደግሞ ቤተክርስቲያንን አይወዱ የነበሩ እንደ ንጉሥ ማርቆስ አረሊስ ዓይነቶች ተነስተው ነበር፡፡

የዓመፅን ሰው አስመልክቶ ሊሰጥ የሚገባው የተሻለ መግለጫ ገና የሚገለጥ አንድ ሰብዓዊ ፍጡር ሲሆን፣ ክርስቶስ ከመመለሱ አስቀድሞ በሚመጣው የመጨረሻ ትውልድ ውስጥ ተፅዕኖ ፈጣሪ የሚሆን፣ ዮሐንስ በ1ኛ ዮሐንስ 2፡18 ውስጥ “ሐሰተኛው ክርስቶስ” ብሎ የሚጠራው ነው፡፡

ምንም እንኳን፣ ምሁራኑ ከላይ ስለጠቀስናቸው ልዩ ልዩ መግለጫዎች ትክክለኛ ትርጓሜ አለመስማማት ቢኖራቸውም፣ ቢያንስ ጳውሎስ ሊያነሳ ስለፈለገው ዋና ነጥብ እርግጠኛ መሆን እንችላለን፡፡ ከተሰሎንቄ ሰዎች አንዳንዶቹ ለክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ከነበራቸው ከመጠን ያለፈ ግለት የተነሳ በጣም ርቀው በመሄድ፣ ኢየሱስ ተመልሷል፣ ስለዚህ ተስፋ እንደተገባላቸው ከእርሱ ጋር የመክበራቸው ነገር አልፎባቸዋል ብለው ያስቡ ነበር፡፡ ስለዚህ፣ ጳውሎስ ክርስቶስ ከመመለሱ አስቀድሞ በርካታ ነገሮች ይከናወናሉ በማለት ነገሩን መፍትሄ ያበጅለታል፡፡ እነዚህ ነገሮች እስካልተፈፀሙ ድረስ፣ ኢየሱስ ተመልሶ እንዳልመጣ ግልፅ ነው ማለት ነው፡፡

ጳውሎስ ስለክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ የሚያመለክተው የተሰሎንቄ ሰዎች ያስቡ ከነበረው እጅግ በራቀ ሁኔታ ሲሆን አሁን ስለሚኖሩበት ሕይወት ዐይናቸውን በሚከፍት መንገድ አቅርቦት ነበር፡፡ በተመሳሳይ መንገድ፣ እኛም ስለክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ቅርብነት በጣም የምናስብ ከሆነ አሁን ስለምንኖረው ሕይወት የግዴለሽነት

ስሜት የመሰማቱ ፈተና ይገጥመናል፡፡ ስለዚህ አሁን በዚህ ዘመን በምንኖረው ሕይወት “የሆነና ገና የሚሆን” በሚለው አስተሳሰብ ውስጥ በመሆን ሃላፊነትና ትግል እንዳለብን ልናስታውስ ይገባናል፡፡

# 5. ማጠቃለያ

በዚህ ትምህርት በተሰሎንቄ ቤተክርስቲያን ውስጥ ተነስተው ለነበሩ ችግሮች ጳውሎስ እንዴት ምላሽ እንደሰጠ ተመልክተናል፡፡ ከተሰሎንቄ ሰዎች ጋር የነበረውን ግንኙነት ዳራ መርምረናል፡፡ ለተሰሎንቄ ሰዎች የጻፋቸውን መልእክቶች ይዘት ዳስሰናል፡፡ በመጨረሻም፣ በተሰሎንቄ ተነስቶ ለነበረው ችግር ጳውሎስ ነገረ-መለኮቱን በማዛመድ እንዴት ምላሽ እንደሰጠ ማለትም ያለ መጠን የጋለውን ነገረ-ፍፃሜአቸውን ቀዝቀዝ በማድረግ አሁን እዚህ ወደሚኖሩበት ሕይወት ትኩረታቸውን እንደሳበው አይተናል፡፡

ጳውሎስ ለተሰሎንቄ ሰዎች በሰጠው ምላሽ ውስጥ፣ ነገረ-ፍፃሜው በርካታ ተግባራዊ ችግሮቻቸውን እንዴት እንዳቃለላቸው አይተናል፣ ዛሬም እኛን አቅጣጫ ያስይዘናል፡፡ ዛሬም በርካታ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ዳግመኛ መመለስ ረገድ ያልተገባ ትኩረት በማድረግ አሁን የሚኖሩበትን ዘመን ወሳኝነት ቸል ይላሉ፡፡ ክርስቶስ ግን በመንግሥቱ ውስጥ አሁን ያለብንን ሃላፊነት ምንም እርባና እንደሌለው አድርገን እንድንቆጥረው አይፈልግም፡፡ ይልቁኑ፣ ይህንን ጊዜ ለእርሱ ታማኝ ሆነን የምንዘልቅበት፣ በቅድስና የምናድግበት፣ በዓለምም የእርሱ ምስክሮች የምንሆንበት እንደሆነ እንድናየው ሾሞናል፡፡ ያኔ ድሮ ለተሰሎንቄ ሰዎች እንደተናገረ ሁሉ፣ ዛሬም ቢሆን የጳውሎስ ማዕከላዊ ነገረ-መለኮት ለእኛ ይናገረናል፡፡ የጌታን ዳግመኛ መመለስ እና የመጪውን ዘመን በረከቶች በምንጠባበቅበት ወቅት ታማኞችና የተቀደሱ ሆነን እንድንዘልቅ ያበረታታናል፡፡